# በአርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች
# የጥናቶች
# አገልግሎት እና ፖሊሲዎች የአንደኛ ደረጃ
# ፕሮግራም

# 2022-2023





የጥናቶች አገልግሎት እና ፖሊሲዎች የአንደኛ ደረጃ ፕሮግራም በኤሌክትሮኒክ መንገድ በአርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች ድረ ገጽ ላይ ይገኛል።

ነሐሴ 2022

ወደ አርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች የአንደኛ ደረጃ ጥናቶች ፕሮግራም እንኳን ደሕና መጡ! በአርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች ውስጥ ያለዎትን ተሳትፎ እያደነቅን ለልጅዎ ጠንካራ የሆነ ትምህርታዊ ፕሮግራም ለማቅረብ ቁርጠኞች ነን።

*ይህ ሰነድ፣ ማለትም የአንደኛ ደረጃ ጥናቶች፣ አገልግሎቶች እና ፖሊሲዎች ፕሮግራም*፣ በአርሊንግተን አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞች እና ዝግጁ አገልግሎቶችን በተመለከተ መረጃ ይሰጣል። ግልጽነትና ጥቅልነትን ለማሳካት፣ የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶቻችን በርካታ ክፍሎችን በተመለከተ አጭርና ምክንያታዊ መግለጫዎች ቀርበዋል። ከእነዚህ አርእስት መካከል አብዛኞቹን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ በአርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች ድረ ገጽ ላይ ይገኛል። ተጨማሪ መረጃን የተመለከቱ ጥያቄዎች የሚቀርቡባቸው የስልክ ቁጥሮችም ቀርበዋል።

*የአንደኛ ደረጃ ጥናቶች፣ አገልግሎቶች እና ፖሊሲዎች* ፕሮግራም አርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች የሚከተሉትን በተመለከተ ያለውን ቁርጠኝነት ያንጸባርቃል፡-

- እያንዳንዱ ተማሪ ለስኬት በሚያበቁ የተለያዩ መንገዶች የሚፈተንና የሚሳተፍ መሆኑን ለማረጋገጥ
- ጤናማ፣ አስተማማኝና ደጋፊ በሆነ የማስተማሪያ አካባቢ ውስጥ የሁሉንም ተማሪዎች አስተውሎታዊ፣ አካላዊ፣ አእምሯዊ እና ማሕበረ-ስሜታዊ ዕድገትን ለመኮትኮት
- ተማሪዎች በትምህርታዊ ተሞክሯቸው ውስጥና በቀጣይ እርምጃዎች ስኬታማ እንዲሆኑ ለማዘጋጀት
- የተማሪዎችን ፍላጎቶች የሚያስተናግዱ ተጨማሪ አገልግሎቶችን በማቅረብ የተማሪዎችን የመማር ሒደት መደገፍ

በገለጻ መስጫ፣ ከእረፍት በኋላ ወደ ት/ቤት የመመለሻ ምሽት፣ በኮንፈረንሶችና ሌሎች ቀጠሮ ተይዞላቸው በሚካሄዱ አጋጣሚዎች ላይ ከት/ቤቱ ርዕሰ መምህር ጋር መረጃ እንዲለዋወጡና እንዲገናኙ እናበረታታዎታለን። ስልክ ደውለው የብቻዎት ቀጠሮ እንዲያዝልዎት ማድረግም ይችላሉ።

በአርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች ውስጥ ከእኛ ጋር ስለተገናኙና ፖሊሲዎቻችንን፣ ፕሮግራሞቻችንን እና አገልግሎቶቻችንን ስለዳሰሱ እናመሰግናለን። እባክዎ በልጅዎ ትምህርት ውስጥ ያለዎትን ተሳትፎ ይቀጥሉ። ቡድናችን የልጅዎን ትምህርትና ዕድገት ለመደገፍ ከእርስዎ ጋር አብሮ ለመስራት በጉጉት ይጠባበቃል።

አርሊንግተን የህዝብ ትምህርት ቤቶች (Arlington Public Schools)
የአካዳሚክ ጽ/ቤት

# 2022-2023

## ማውጫ


*የፖሊሲ መግለጫዎች* 4

የፖሊሲ መረጃ፡- ቅበላ 5

የፖሊሲ መረጃ፡- የቤት ስራ እና የክረምት ወቅት አሳይመንቶች 6

የፖሊሲ መረጃ፡- ደረጃውን የጠበቀ ምርመራ 6

*የአንደኛ ደረጃ ዕድገት ምዘናዎች ለበልግ ወቅትና ለዓመቱ አጋማሽ* 6

*የአንደኛ ደረጃ SOL ፈተናዎች ለሜይ እና ጁን* 6

የአንደኛ ደረጃ ወደ ት/ቤት መመለሻ ምሽት 8

ደረጃ ላይ የተመሰረተ ሪፖርት አደራረግ 8

ልማዳዊ የውጤት ሪፖርት አደራረግ 9

*1ኛ-2ኛ ክፍሎች ልማዳዊ የውጤት ሪፖርት አደራረግ ለሁሉም የይዘት መስኮች* 10

*ልማዳዊ የውጤት ሪፖርት አደራረግ ለ 3ኛ-5ኛ ክፍል፣ ለቋንቋ ጥበባት (ማንበብ እና መጻፍ)፣ ሒሳብ፣ ሳይንስ፣ እና ማህበራዊ ጥናቶች* 10

የፖሊሲ መረጃ – ወደ ቀጣይ ክፍል ማዛወር እና ማስደገም 11

ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች 11

የፌዴራል እና የስቴት ፕሮግራሞች 11

ሌሎች ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች 11

*የጥናቱ ትምህርታዊ መስኮች* 11

## የፖሊሲ መግለጫዎች

**የአርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች የት/ቤት ቦርድ ፖሊሲዎችን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ ቀጣዩን ማስፈንጠሪያ ይጠቀሙ:-**

https://www.apsva.us/school-board-policies/

### ቅበላ

የአርሊንግተን ካውንቲ ነዋሪ ልጆች እስከ ሴፕቴምበር 30 ድረስ አምስት አመት ከሞላቸው በአርሊንግተን ት/ቤቶች ውስጥ ከክፍያ ነጻ ለመማር ብቁ ናቸው። ወላጆች ልጃቸውን በአጸደ ሕጻናት ውስጥ ለማስመዝገብ ካልፈለጉ፣ ለአካባቢያቸው ት/ቤት ማሳወቅ አለባቸው። ልጆች ዕድሜያቸው ስድስት ዓመት ሲሞላ ት/ቤት መመዝገብ አለባቸው። ተጨማሪ መረጃ ከእንግዳ መቀበያ ማዕከል 703-228-8000 ወይም ከዚህ ማግኘት ይቻላል:- https ://www.apsva.us/registering-your-child/።

በአርሊንግተን ውስጥ ወደሚገኝ አጸደ ሕጻናት ወይም ሌላ የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ለመጀመሪያ ጊዜ የሚገቡ ተማሪዎች የሚከተሉትን ማስረጃዎች ማቅረብ አለባቸው:-

1. የልደት ምስክር ወረቀት ወይም ሌላ የጸና የትውልድ ቀን ማስረጃ።
2. ወደ ት/ቤት ከመግባታቸው በፊት ባሉት 12 ወራት ውስጥ የተካሄደ የአካላዊ ጤና ምርመራ ውጤት።
3. ተላላፊ የጉሮሮ በሽታ (diphtheria)፣ ትክትክ (የማያቋርጥ ሳል)፣ ቴታነስ፣ ፖሊዮ፣ ሄፓታይቲስ ቢ(ስድስተኛ ክፍል ሲደርሱ)፣ ኩፍኝ፣ ጆሮ ደግፍ እና የጀርመን ኩፍኝ (ሩቤላ) በሽታዎች መከላከያ ክትባት የወሰዱበትን ቀን/ወር/ዓመት የሚገልጽ የሕክምና መረጃ (ፈቃድ ካለው ሐኪም የተሰጠ ማስረጃ)።
   - ወደየትኛውም ት/ቤት ለመጀመሪያ ጊዜ ሲገቡ የኩፍኝ፣ ጆሮ ደግፍ እና የጀርመን ኩፍኝ (ሩቤላ) በሽታዎች መከላከያ ሁለተኛ ዙር ክትባት የወሰዱበትን ቀን/ወር/ዓመት የሚገልጽ ማስረጃ (ፈቃድ ካለው ሐኪም የተሰጠ ማስረጃ)።
   - ወደ አርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤት ከመግባቱ ባለው አንድ ዓመት ውስጥ ወይም በምዝገባ ወቅት ከነበረ የእረፍት ቆይታ በኋላ የተካሄደ የቲዩበርኩሊን ቆዳ ምርመራ ውጤት የጽሁፍ ማስረጃ።
   - በሃይማኖታቸው ምክንያት ክትባትን የማይደግፉ ቤተሰቦች በልዩ የቨርጂኒያ ግዛት ቅጽ ላይ በውል አዋዋይ የተረጋገጠ መግለጫ ማቅረብ አለባቸው፤ ቅጹን ከት/ቤቱ ማግኘት ይቻላል። በተጨማሪም፣ አስፈላጊ ከሆኑት ክትባቶች መካከል አንዱ ወይም ከአንድ በላይ ለልጁ ጤና ጎጂ ከሆነ፣ በጤና ምክንያት ከክትባት ውጭ የሚያደርግ ፈቃድ በሐኪም መፈረም አለበት።
4. የመኖሪያ አድራሻ ማስረጃ ወይም በስልሳ (60) የመቁጠሪያ ቀናት ውስጥ መኖሪያን ወደ አርሊንግተን ስለመቀየሩ ማስረጃ መቅረብ አለበት። የመኖሪያ አድራሻ ማስረጃ የሚባሉት መካከል በአከራይ እና ተከራይ የተፈረመ የኪራይ ውል ወይም ወላጅ/አሳዳጊ የቤት ባለቤት መሆናቸውንና በአርሊንግተን ካውንቲ ውስጥ እንደሚኖሩ የሚያሳይ የሞርጌጅ ስምምነት ቅጂ ይገኙበታል። በዚህ ውስጥ የማይካተቱ ልዩ ሁኔታዎች በአርሊንግተን ት/ቤት ፖሊሲዎች ውስጥ ተዘርዝረዋል። የአርሊንግተን ት/ቤት ፖሊሲዎች በእያንዳንዱ ት/ቤት ውስጥ፣ በሲፋክስ የትምህርት ማዕከል (Syphax Education Center) እና በሕዝብ ቤተ መጻሕፍት እና በዚህ ድረ ገጽ ላይ ይገኛሉ:- https://www.apsva.us/school-board-policies/

***ልጅዎ መማር ያለበት የትኛው ት/ቤት ውስጥ መሆኑን ለማወቅ፤ ለአርሊ ንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች እና የማህበረሰብ ግንኙነት ቢሮ በስልክ ቁጥር 703-228-6005 ይደውሉ ወይም በቀጣዩ ድረ ገጽ ላይ ያለውን ኢጋዥ መረጃ ይጠቀሙ:-*** https://www.apsva.us/boundary-locator/.

### የቤት ስራ

የአርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች ተማሪዎች እንዲለማመዱ፣ እንዲዘጋጁ፣ እንዲያጠኑ እና/ወይም ትምህርትን እንዲያሰፉ የሚያስችሉ በምርምር ላይ የተመሰረቱ ተመጣጣኝ የቤት ስራ ልምምዶችን ይደግፋል። የቤት ስራ ከይዘት ደረጃዎች ጋር መጣጣም ያለበት ሲሆን ሁሉም ተማሪዎች ተጨማሪ ኢጋዥ ማቴሪያል ወይም የአዋቂ ሰው ከፍተኛ ድጋፍ ሳያስፈልጋቸው ሊሰሯቸው የሚገቡ መሆን አለባቸው። መምህሩ ለቤት ስራ ነጥብ በሚሰጥበት ወቅት የሚያተኩረው ተማሪው በተሰጠው የትምህርት ይዘት ላይ እውቀትና ክህሎትን በተግባር ማሳየቱ ላይ ነው፤ ውጤቱም በወቅቱ ታርሞ፣ ወጥነትን በጠበቀ መልኩ ለተማሪዎችና ወላጆች በግልጽና መደበኛ በሆነ መንገድ መገለጽ አለበት። የቤት ስራ ላይ የሚደረግ ምዘና የአንድን ተማሪ ባህሪ ምዘናን አያንጸባርቅም።

የቤት ስራ:-

- ቅድሚያ የሚሰጠው ቀድሞ የተማሩትን ነገር ለማስረጽና አግባብነት ሲኖረውም ትምህርትን ለማስፋት ነው።
- ለተማሪዎች እና ወላጆች/አሳዳጊዎች በግልጽ መላክ አለበት።
- ለተማሪው ዕድሜና የዕድገት ሁኔታ የሚመጥን መሆን አለበት
- ውስን የሆነ ጊዜ የሚፈልግና በተማሪው እንቅስቃሴዎች ውስጥ የሚፈጥረው መስተጓጎል መጠነኛ መሆን አለበት
- በቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ ውስጥ በተገለጸው መሰረት የተማሪዎች ስኬትን እያዳበረ እስከ ምርቃት የሚያደርስ ነው፤ ይህም የሚሳካው በሚከተሉት መንገዶች ነው:-
  - በጥልቀት የማሰብ ክህሎቶች
  - ፈጠራዊ የአስተሳሰብ ክህሎቶች
  - የተግባቦት ክህሎቶች
  - የትብብር ክህሎቶች
  - የዜግነት ክህሎቶች

## የፖሊሲ መግለጫዎች

አንድ ተማሪ አንድን አሳይመንት ለማጠናቀቅ ይፈጅበታል ተብሎ የሚጠበቅ ከፍተኛው የጊዜ መጠን በቀጣዮቹ መመሪያዎች ውስጥ የቀረበ ነው። መምህሩ የቅድሚያ ማስታወቂያ በመስጠት ለማጠናቀቅ ተጨማሪ ጊዜ የሚፈልጉ የረዥም ጊዜ አሳይመንቶችንም ሊሰጥ ይችላል። በየትኛውም ምሽት መምህራን በአንድ የትምህርት ይዘት ላይ ያተኮረ የቤት ስራ አይሰጡም።

| የክፍል ደረጃ | መመሪያዎች |
|---|---|
| **K** | ከ30 ደቂቃ በላይ የማይፈጅ ማንበብና መጻፍ እና/ወይም ቀላል ሒሳቦችን ማስላት (ራስን ችሎ ማንበብ ወይም ሌላ ሰው ሲያነብብ ማዳመጥን ጨምሮ) |
| **1** | ከ30 ደቂቃ በላይ የማይፈጅ ማንበብና መጻፍ እና/ወይም ቀላል ሒሳቦችን ማስላት (ራስን ችሎ ማንበብ ወይም ሌላ ሰው ሲያነብብ ማዳመጥን ጨምሮ) |
| **2** | ከ30 ደቂቃ በላይ የማይፈጅ ማንበብና መጻፍ እና/ወይም ቀላል ሒሳቦችን ማስላት (ራስን ችሎ ማንበብ ወይም ሌላ ሰው ሲያነብብ ማዳመጥን ጨምሮ) |
| **3** | ከ45 ደቂቃ በላይ የማይፈጅ (ራስን ችሎ ማንበብን ጨምሮ) |
| **4** | ከ60 ደቂቃ በላይ የማይፈጅ (ራስን ችሎ ማንበብን ጨምሮ)፤ እንደ አግባብነቱም የመሳሪያ ብቻ የተቀነባበረ ሙዚቃ ለመለማመድ ተጨማሪ 15 ደቂቃ |
| **5** | ከ60 ደቂቃ በላይ የማይፈጅ (ራስን ችሎ ማንበብን ጨምሮ)፤ እንደ አግባብነቱም የመሳሪያ ብቻ የተቀነባበረ ሙዚቃ ለመለማመድ ተጨማሪ 15 ደቂቃ |

### <u>የቤት ስራን የሚመለከቱ መመሪያዎች ለመምህራን</u>

መምህራን መስጠት ያለባቸው የቤት ስራ ተማሪዎች እንዲለማመዱ፣ እንዲዘጋጁ፣ እንዲያጠኑና ትምህርትን እንዲያሰፉ የሚያስችላቸው መሆን አለበት። መምህራን የቤት ስራን መስጠት ያለባቸው በባህሪይ ላይ ውጤት በሚያስከትል መንገድ መሆን የለበትም።

የቤት ስራ ሲሰጥ በተቻለ መጠን በትምህርት ዓይነቶች፣ በቡድኖች፣ በመምህራን እና/ወይም በክፍል ደረጃዎች መካከል ቅንጅት መፈጠር አለበት፤ ይህም የስራ ጫናን ለመላው የትምህርት መስክ ለማከፋፈል፣ አሳይመንቶችን ለማጠናቀር እና በየትኛውም ምሽት ላይ ከመጠን ያለፈ ጊዜን ለማስቀረት ያስችላል።

የቤት ስራ ሲዘጋጅ የሁሉንም ተማሪዎች የተለያዩ ፍላጎቶች እንዲያካትት ተደርጎ መሆን አለበት፤ ይህም የእንግሊዝኛ ተማሪዎች፣ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች፣ እንዳግባብነቱና እንዳስፈላጊነቱ ልዩ ስጦታ ላላቸው ይዘቶች የተለዩ ተማሪዎችን ይጨምራል። አንድ ተማሪ ግለሰባዊ የትምህርት ዕቅድ (IEP) ወይም 504 ዕቅድ ሲኖረው፣ አስፈላጊ ማሻሻያዎችና መስተንግዶዎችን መከተል ያስፈልጋል።

ከመምህሩ የሚሰጥ ግብረ መልስ የሚያተኩረው ተማሪዎች በተሰጠው የትምህርት ይዘት ላይ እውቀትና ክህሎትን በተግባር ማሳየታቸው ላይ ነው፤ ውጤቱም በወቅቱ ታርሞ፣ ወጥነትን በጠበቀ መልኩ ለተማሪዎችና ወላጆች/አሳዳጊዎች በግልጽና መደበኛ በሆነ መንገድ መገለጽ አለበት። መምህራን ተማሪዎች ለቤት ስራ የሚሰጡትን ምላሽ አይተው የወደፊት ትምህርታዊ ውሳኔዎችን እንዲወስኑ ያግዛቸው ዘንድ ይጠቀሙበታል። ባጠቃላይ፣ የቤት ስራን ግንዛቤ ለመመዘን ጥቅም ላይ መዋል ያለበት የትምህርት ጊዜ አጭር መሆን አለበት። የቤት ስራ ምዘና የአንድን ተማሪ ባህሪይ ግመገማ አያንጸባርቅም።

### <u>የቤት ስራን የሚመለከቱ መመሪያዎች ለወላጆች</u>

ወላጆች/አሳዳጊዎች የአርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች ፖሊሲ I-11.2 የቤት ስራ እና የፖሊሲ ትግበራ አሰራር I-11.2 PIP-1 የቤት ስራ እና ተማሪዎቻቸው የሚማሩበት ት/ቤት እና መምህራን የሚያስቀምጡትን ግዴታ ማወቅ አለባቸው። ወላጆች/አሳዳጊዎችም በተቻለ መጠን የተሰጡ የቤት ስራዎች መጠናቀቃቸውን ከተማሪያቸው ማጣራት አለባቸው። አንድ ተማሪ የቤት ስራ በመስራት ከመጠን ያለፉ ጊዜ ካጠፋ (ገጽ አንድ ላይ በተጠቀሰው መሰረት)፣ ወላጅ/አሳዳጊ ለመምህሩ ማሳወቅ አለበት፤ ይህም መምህሩ ተገቢው ድጋፍ ምን እንደሆነ ለመወሰን ተማሪውን እና ወላጅ/አሳዳጊን ለማገዝ ያስችለዋል።

### <u>የበጋ ወቅት አሳይመንቶች</u>

በበጋ ወቅት የሚሰጡ አሳይመንቶች ለመለማመድ፣ ለመዘጋጀት፣ ለማጥናት እና/ወይም ትምህርትን ለማስፋት ያገለግላሉ። በአንደኛ ደረጃ ትምህርት፣ የበጋ ወቅት አሳይመንቶች አማራጭ ስርዓት አቀፍ አሳይመንቶች ላይ የተገደቡ ሲሆን፣ አጠቃላይ የት/ቤት ፕሮግራሞችም የሚያኩሩት ማንበብና መጻፍና ቀላል የሒሳብ ስሌቶች ድጋፍ ላይ ነው። ስርዓት አቀፍ አሳይመንቶች በአርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች የይዘት ክፍል ተዘጋጅተው ለሁሉም ተማሪዎች እንደየክፍል ደረጃቸው ይሰራጫሉ (ለምሳሌ፦ የበጋ ወቅት የሒሳብ ዳሰሳ)። በይዘት አካባቢ አማራጭ የስርዓት አቀፍ አሳይመንቶች የሚዘጋጁት በማዕከላዊ ቢሮ ሰራተኞች ነው። እንደዚህ ዓይነት አሳይመንቶች በት/ቤት ሰራተኞች የሚሰራጩ ሲሆኑ፣ የሚዘጋጁበት ዓላማም ተማሪዎች ባለፈው የትምህርት ዘመን የተማሯቸውን ፅንሰ ሃሳቦችና ክህሎቶች ለመዳሰስ እድል እንዲያገኙ ማድረግና በቀጣዩ የትምህርት ዘመን ለሚተዋወቁ ጽንሰ ሃሳቦችና ክህሎቶች እንዲዘጋጁ ማድረግ ነው። የበጋ ወቅት አሳይመነቶችን በተመለከተ ተጨማሪ ዝርዝር መረጃዎች [የፖሊሲ ትግበራ አሰራር I-11.2 PIP-2 የበጋ ወቅት አሳይመንቶች ውስጥ ተቀምጠዋል።tie]

መምህራን የተለዩ ኢጋዥ ግብዓቶች (ኮምፒዩተሮች፣ ሶፍትዌር፣ የተወሰኑ መጽሐፍት፣ የገንዘብ ወጪ) የሚያስፈልገው የበጋ ወቅት የቤት ስራ ከሰጡ፣ ት/ቤቱ ሁሉም ተማሪዎች የቤተሰባቸው ሁኔታ እና/ወይም የበጋ ወቅት እቅዳቸው ምንም ቢሆን ተመጣጣኝ ተደራሽነትን በሚያረጋግጥ መንገድ እነዚህን ግብዓቶች የማቅረብ ወይም

ተደራሽነታቸውን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት። እነዚህ አሳይመንቶች የሚዘጋጁበት ዓላማ ተማሪዎች ባለፈው የትምህርት ዘመን የተማሯቸውን ፅንሰ ሃሳቦችና ክህሎቶች ለመዳሰስ እድል እንዲያገኙ ማድረግና በቀጣዩ የትምህርት ዘመን ለሚተዋወቁ ጽንሰ ሃሳቦችና ክህሎቶች እንዲዘጋጁ ማድረግ ነው። እነዚህ አሳይመንቶች ትምህርት በተጀመረ የመጀመሪያ ሳምንት ውስጥ ተሰብስበው ትምህርት በተጀመረ የመጀመሪያ ሳምንት ውስጥ ምቹ በሆነ የመማሪያ ክፍል ውስጥ በመምህራንና ተማሪዎች መታረም አለበት። በአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ፣ ተማሪዎች ፖዘቲቭ ክሬዲት እና እውቅና ሊሰጣቸው ይገባል፤ አሳይመንቶች ወይም የአሳይመንት አለመኖር በአንድ ተማሪ ውጤት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ማሳደር የለበትም።

## የፖሊሲ መግለጫዎች

**ማካካሻ**

በት/ቤት ውስጥ በሚጠበቅባቸው መጠን በማንኛውም ምክንያት እመርታ የማያሳዩ ተማሪዎች በተለያዩ የት/ቤት እና ስርዓት አቀፍ የመከላከያ፣ ጣልቃ መግባት እና/ወይም የማካካሻ ፕሮግራሞች ውስጥ የመሳተፍ እድል አላቸው። የአንድ ተማሪ እመርታ የሚመዘነው የተለያዩ ዓይነት መስፈርቶችን በመጠቀም ሲሆን፣ ደረጃ የወጣላቸው ፈተናዎች ላይ የነበረ አፈጻጸም፣ ደረጃ ከወጣላቸው ፈተናዎች ጋር የተያያዙ መተንበያ ፈተናዎች፣ የመማሪያ ክፍል የስርዓተ ትምህርት ምዘናዎች፣ የወላጅ/ተንከባካቢ ምልከታና የመምህር ምልከታም በዚህ ውስጥ ይካተታሉ። ወላጆች የተማሪዎችን እመርታ በተመለከተ የሚካሄዱ ቀጣይ ምዘናዎችን አስመልክቶ መረጃዎች በትምህርት ዘመኑ ውስጥ በተለያየ መንገድ (ኮንፈረንሶች፣ ሪፖርት ካርዶች፣ ሳምንታዊ በቦርሳ ውስጥ የሚላክ መልእክት) ይደርሳቸዋል። 3ኛ፣ 4ኛ እና 5ኛ ክፍል ላይ የSOL ፈተናዎችን የወደቁ ተማሪዎች ልዩ ፕሮግራሞች ላይ መሳተፍ ሊኖርባቸው ይችላል፤ ምናልባትም የተራዘመ የትምህርት ቀን ወይም አስገዳጅ የበጋ ጊዜ ትምህርትን ሊያካትት ይችላል። የ3ኛ ወይም 4ኛ ክፍል ንባብ እና/ወይም የሒሳብ SOL ፈተናዎችን የወደቁ ተማሪዎች እንደ ቅደም ተከተላቸው ወደ 4ኛ ወይም 5ኛ ክፍል ሲገቡ የማካካሻ ትምህርት ላይ ሊሳተፉ ይችላሉ።

**በአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ ያለ ደረጃውን የጠበቀ ፈተና አሰጣጥ**

የቨርጂኒያ የትምህርት ቦርድ የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች በትምህርት ደረጃዎች (SOL) ምዘና ላይ እንዲሳተፉ ይጠይቃል። የSOL ምዘናዎች የቨርጂኒያ SOLን ለማሟላት የተዘጋጁ መስፈርት ተኮር ፈተናዎች ናቸው። የSOL ምዘናዎች የሚካሄዱት ቨርጂኒያ ውስጥ በሚገኙ ሁሉም የሕዝብ ት/ቤቶች ውስጥ በፀደይ ወቅት ነው። የ3ኛ፣ 4ኛ እና 5ኛ ክፍል ተማሪዎች የSOL ፈተናዎችን ይወስዳሉ። ተጨማሪ ፖሊሲ ነክ መረጃ እዚህ ይገኛል፡- https://go.boarddocs.com/vsba/arlington/Board.nsf/files/CCYR7U6C4199/$file/I-1.32%20PIP-1%20Standards%20of%20Learning%20Assessments.pdf

**የአንደኛ ደረጃ ዕድገት ምዘናዎች ለበልግ ወቅትና ለዓመቱ አጋማሽ**

| | ማንበብ | ሒሳብ |
|---|---|---|
| የክፍል ደረጃ | 3,4,5 | 3,4,5 |

**የአንደኛ ደረጃ SOL ፈተናዎች ለሜይ እና ጁን**

| | ማንበብ | ታሪክ | ሒሳብ | ሳይንስ |
|---|---|---|---|---|
| የክፍል ደረጃ | 3,4,5 | 4 | 3,4,5 | 5 |

ወላጆች የእያንዳንዱን ተማሪ ሪፖርቶች በParentVue ላይ ማግኘት ይችላሉ። የአርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች እና የእያንዳንዱ ት/ቤት የማጠቃለያ ውጤቶች በየዓመቱ የሚታተሙ ሲሆን በአርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች ድረ ገጽ ላይ ማግኘት ይቻላል። የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ የት/ቤት አፈጻጸም ሪፖርት ካርድ በየዓመቱ የሚያሳትም ሲሆን ይህም የእያንዳንዱን ት/ቤት የትምህርት ደረጃ ፈተና አፈጻጸም በተመለከተ መረጃ ይሰጣል። እነዚህ የሪፖርት ካርዶች በቀጣዩ የግዛቱ ድረ ገጽ ላይ ይለጠፋሉ፡- http://www.schoolquality.virginia.gov።

የአርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች ዓመቱን በሙሉ መደበኛ በሆነ የጊዜ ልዩነት የማንበብና መጻፍ እና የሒሳብ ምዘናዎችን በቅድመ 5ኛ ክፍል ላይ ያካሂዳል። እነዚህ ምዘናዎች የሚዘጋጁት የተማሪዎችን የሒሳብ እና የማንበብና መጻፍ ክህሎቶች በመመዘን የትምህርት አሰጣጡን ለመወሰንና ከማራዘሚያ እና/ወይም ጣልቃ ገብነት ተጠቃሚ የሚሆኑትን ተማሪዎች ለመወሰን ነው።

## የፖሊሲ መግለጫዎች

ለማስተማሪያነት የሚውሉ አጋዥ ግብዓቶች

የአርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች በሁሉም የክፍል ደረጃዎች ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች መሰረት የሚያስይዙና የተወሰኑ ተጨማሪ አጋዥ ግብዓቶችን ከክፍያ ነጻ ያቀርባል። የት/ቤት ቦርድ የመማሪያ መጽሐፍትን ጨምሮ መሰረት የሚያስይዙ አጋዥ ግብዓቶችን በግዛት መመሪያዎች መሰረት የተቀመጠውን የጊዜ ሰሌዳ አክብሮ ሰራተኞችና የማህበረሰብ አባላትን ያቀፉ አጽዳቂ ኮሚቴዎች የሚሰጡትን ምክረ ሃሳብ ተከትሎ ያጸድቃል። ቦርዱ ምክረ ሃሳቦችን የሚመዝነው በሚከተሉት ላይ ተመስርቶ ነው፡-

- ስኮላርሺፕ፣ የማስተማሪያ ዘዴዎች እና ቴክኒኮች፤
- የአፀደ ሕጻናት-12 ስርዓተ ትምህርት ግቦች እና ወሰን እና ቅደም ተከተል ጋር መጣጣም
- ከኮርሱ ወይም ከሚመለከተው የክፍል ደረጃ ግቦችና ዓላማዎች ጋር ያለ ተዛምዶ፤
- የማሕበራዊ ጉዳዮች እና የባሕል፣ የብሔር እና የቋንቋ ብዝሃነት አያያዝ፤ እና
- አጋዥ ግብዓቶችን በሚገባ መጠቀም።

የመማሪያ መፅሐፍትን ጨምሮ፣ መሰረት የሚጥሉ አጋዥ ግብዓቶች የሚባሉት በግዛቱ የትምህርት ቦርድ እና/ወይም በት/ቤት ቦርድ ተለይተው የተቀመጡና አብዛኞቹ ተማሪዎች በትምህርታቸው ላይ ይጠቀሙባቸዋል ተብለው የሚጠበቁ ናቸው።

ተጨማሪ ማቴሪያሎች ማለት አንድ የትምህርት ክፍል መሰረት ጣይ ከሆኑ አጋዥ ግብዓቶች በተጨማሪ ለአጭር ጊዜ የሚጠቀምባቸው ወይም ትምህርትን የተናጠል ለማድረግ የሚያገለግሉ ናቸው። ተጨማሪ ማቴሪያሎች ስርዓት አቀፍ ወይም ት/ቤት ተኮር ሊሆኑ ይችላሉ። በሁለቱም በኩል፣ በት/ቤት ውስጥ የሚያገለግሉ እንዲህ ዓይነት ማቴሪያሎች በሙሉ በፖሊሲ ትግበራ አሰራሮች ውስጥ የተዘረዘሩ ሒደቶችን በመከተል መፅደቅ አለባቸው።

## የፖሊሲ መግለጫዎች - ለወላጆች ሪፖርት ማድረግ

### የአንደኛ ደረጃ ወደ ት/ቤት መመለሻ ምሽት

ወላጆችና መምህራን የሚሳተፉበት ወደ ት/ቤት የመመለሻ ምሽት ፕሮግራም የበልገ ወቅት የወላጅና መምህራን ኮንፈረንስ ከመካሄዱ በፊት በትምህርት ዘመኑ መጀመሪያ ላይ ይካሄዳል። የስርዓት አቀፍ ፕሮግራም ቢጋሮችን ጨምሮ የጽሑፍ መግለጫ፣ ለማስተማሪያነት የሚያገለግሉ ማቴሪያሎች ዝርዝርና ደረጃ የወጣላቸው ፈተናዎች መርሃ ግብር በመምህሩ ተዘጋጅቶ የበልግ ወቅት ፕሮግራም ከመካሄዱ በፊት ወደ ቤት ይላካል ወይም በፕሮግራሙ ላይ ይሰራጫል ወይም ትምህርት በተጀመረበት የመጀመሪያ ወር ላይ ይላካል። ተማሪዎች በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ላይ እያሉ የሚያሳኩት የተወሰነ የክፍል ደረጃ ላይ የተመሰረቱ ዓላማዎች በእያንዳንዱ ት/ቤት ውስጥ ባሉ ማቴሪያሎች በዝርዝር ተቀምጠዋል።

- የጥናቶች፣ አገልግሎቶች እና ፖሊሲዎች የአንደኛ ደረጃ ፕሮግራም የመረጃ ጥራዝ
- የትምህርት ደረጃዎችን የሚያካትት የስርዓት ትምህርት መምሪያዎች በእያንዳንዱ የይዘት መስክ ውስጥ
- ለማስተማሪያነት የሚውል አጋዥ ግብዓቶች
- የቨርጂኒያ የሕዝብ ት/ቤቶች የመማር ደረጃዎች (SOL)

የወላጆችና መምህራን መድረክ ዓላማው ወደ ቤት የተላከው የጽሑፍ መግለጫ ላይ ለመወያየት፣ ለዓመቱ የተያዙ ማናቸውንም ልዩ የፕሮግራም እቅዶች ለመግለጽ፣ የቤት ስራ ፖሊሲ ላይ ለመወያየት እና ለማስተማሪያነት የሚውሉ ማቴሪያሎችን ለማጋራት ነው።

### የተማሪ እመርታ እና ውጤቶችን ሪፖርት ማድረግ

ሱፐርኢንቴንደንት እና ሰራተኞች በእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ የሚያገለግሉ የሪፖርት ማድረጊያ እቅዶችን አዘጋጅተው ቦርዱ እንዲያጸድቀው ያደርጋሉ። በዋና ሕንጻዎች ውስጥ የሚሰሩት የአካዳሚክስ ሃላፊ እና የት/ት ድጋፍ ሃላፊ ሪፖርት ማድረጊያ እቅዶችን የመንደፍና የመተግበር ሃላፊነት አለባቸው። መምህራን የእያንዳንዱን ተማሪ ስኬቶች ዝርዝርና ስልታዊ መረጃዎችን በመያዝ ተማሪው በተመዘገበበት የክፍል ደረጃ የተዘጋጀ ሪፖርት ማድረጊያ ቅጽን ተጠቅመው የእያንዳንዱን ተማሪ እመርታ በተወሰነ ወቅት ለወላጆች/አሳዳጊዎች ሪፖርት ያደርጋሉ። ከዓመታዊ የውጤት ማሳወቂያ ሪፖርቶች በስተቀር፣ መምህራን የፈተና ማረሚያ ጊዜ ካበቃ በኋላ የፈተና ውጤቶችን ለማቅረቢያ ቢያንስ ሁለት ሙሉ የትምህርት ቀናት አላቸው።

#### ለወላጆች/አሳዳጊዎች መረጃ የሚሰጥባቸው አሰራሮች እና መመሪያዎች

"በእያንዳንዱ የትምህርት ዘመን መጀመሪያ፣ እያንዳንዱ ት/ቤት የሚከተሉትን ጉዳዮች ዝግጁ መሆን እና የመገኛ ምንጭን የተመለከቱ መረጃዎችን ለተማሪዎቹ፣ ለወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ያቀርባል፡-

- በ8 VAC 20-131-70 ድንጋጌዎች መሰረት የተዘጋጁና በልጆች የክፍል ደረጃ ወይም በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ላይ የሚሳኩ የትምህርት ዓላማዎች፣ ልጆቻቸው የሚማሩትን እያንዳንዱን ኮርስ መርሃ ትምህርት ቅጂ እና የት/ቤት መምሪያው ወደ ቀጣይ ክፍል ማሳለፊያ፣ ክፍል ማስደገሚያ እና የማካካሻ ፖሊሲዎች ቅጂ፤
- የዚህ ልጅ የክፍል ደረጃ ላይ ተፈጻሚነት ያላቸው የመማር ደረጃዎች ወይም ኮርሱ የሚጠይቃቸው ሁኔታዎችና የልጁ ቀጣይ SOL ፈተና የሚሰጥበት ግምታዊ ቀንና ሊያሳድር የሚችለው ተጽእኖ፤ እና
- በሁሉም የክፍል ደረጃዎች ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች ለስታንዳርድ እና አድቫንስድ ስተዲስ ዲፕሎማዎች የሚያስፈልጉ መስፈርቶችና ቦርዱ በ 8 VAC 20-131-30 ስር በተደነገገው መሰረት ያሉት የትምህርት ክፍል ዝውውርና እዚያው ክፍል ውስጥ የማስቀረት ፖሊሲዎችን የተመለከተ ዓመታዊ ማስታወቂያ። የመምሪያው ሱፐርኢንቴንደንት በ 8VAC20-131-390 A." (8 VAC 20-131-270) በተደነገገው መሰረት ይህ ንኡስ ክፍል መከበሩን ለቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ ሪፖርት ያደርጋል።

#### የተማሪን ስኬት ማሳወቅ እና መመዘን

እያንዳንዱ የትምህርት ዘመን ከመጀመሩ በፊት፣ እያንዳንዱ መምህር የተማሪዎችን የኮርስ ውጤቶች ለመወሰን የሚያገለግሉ ደረጃዎችና መስፈርቶችን የሚያስቀምጥ ሲሆን፣ ይህን ሲያደርግም ደረጃዎች እና ዓላማዎችን በአርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች ስርዓት ትምህርት ውስጥ በማካተትና በእያንዳንዱ የስርዓተ ትምህርት መስክ ውስጥ በሚኖር ስርዓት አቀፍ አቅጣጫ መሰረት ነው። እነዚህ ደረጃዎችና አስፈላጊ መስፈርቶች በትምህርት ዘመኑ መጀመሪያ ላይ ለተማሪዎች እና ወላጆች/አሳዳጊዎች ይቀርባሉ። የተማሪ ውጤቶች የሚያንጸባርቁት የተማሪውን ስኬት እንጂ ባህሪይ አይደለም።

በዲስትሪክት የተቀመጡ መነሻ ምዘናዎች ላይ የሚታይ የተማሪ አፈጻጸም ብቃት ለወላጆች/አሳዳጊዎች ሪፖርት የሚደረግ ሲሆን የተማሪዎችን ውጤት ለማስላትም አይካተትም።

#### ለአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ወላጆች/አሳዳጊዎች ሪፖርት ማድረግ

ሁሉም ወላጆች/አሳዳጊዎች የእመርታ ሪፖርት ይደርሳቸዋል። ሱፐርኢንቴንደንት በአንደኛ ደረጃ ላይ ሁለት ሪፖርት ማድረጊያ ስርዓቶችን አጽድቀዋል፣ እነርሱም ደረጃ ላይ የተመሰረተ እና ልማዳዊ ናቸው። የእያንዳንዱ ስርዓት መግለጫ ከታች ቀርቧል። ከአንድ የተፈቀደ የውጤት አሰጣጥ ስርዓት ወደ ሌላ የመቀየር ውሳኔ የሚወሰነው በሱፐርኢንቴንደንት ሆኖ የት/ቤት ሰራተኞችን ጨምሮ ከት/ቤቱ ማህበረሰብ የሚያገኘውን ግብዓት ይጠቀማል፤ በት/ቤቱ ማህበረሰብ፣ ፔዳጎጂ እና ምዘና ላይ የተመሰረተ መሆንም አለበት።

## የፖሊሲ መግለጫዎች - ለወላጆች ሪፖርት ማድረግ

### ደረጃ ላይ የተመሰረተ የውጤት ሪፖርት አደራረግ K-5

ከአፀደ ሕጻናት እስከ አምስተኛ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎች ለእንግሊዝኛ ቋንቋ አርትስ (ማንበብ/መጻፍ)፣ ሒሳብ፣ ሳይንስ፣ ማሕበራዊ ጥናቶች፣ አርት፣ ሙዚቃ እና የአካል ማጎልመሻ ትምህርቶችን በደረጃ ላይ የተመሰረተ የእምርታ ሪፖርት ይሰጣቸዋል። የአፀደ ሕጻናት ተማሪዎች ሪፖርቱን በዓመት ሁለት ጊዜ የሚያገኙ ሲሆን፣ ከ1ኛ እስከ 5ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች ደግሞ የሩብ ዓመት ሪፖርት ይሰጣቸዋል።

በዘጠኝ ሳምንታት ውስጥ አራት የጽሑፍ ሪፖርቶች እንዲቀርቡ የጊዜ ሰሌዳ ይወጣል። ሁለት የወላጅ/አሳዳጊ እና መምህራን ኮንፈረንሶችም የጊዜ ሰሌዳ ይወጣላቸዋል - አንዱ በበልግ ወቅት እና ሌላው በፀደይ ወቅት። የመጀመሪያው ኮንፈረንስ የሚካሄደው ት/ቤት መከፈቻ ጊዜ እና የመጀመሪያ የጽሑፍ ሪፖርት በሚዘጋጅበት ጊዜ መካከል ነው። ሁለተኛው ኮንፈረንስ የሚካሄደው ደግሞ በሁለተኛ እና ሶስተኛ የጽሑፍ ሪፖርቶች መካከል ነው።

የወላጅ/አሳዳጊ እና መምህራን ኮንፈረንሶች የጊዜ ሰሌዳ የሚወጣላቸው በቀጠሮ ላይ ተመስርቶ ነው። የበልግ ወቅት ኮንፈረንሶች ከመካሄዳቸው በፊት፣ ስርዓት አቀፍ የፕሮግራም ቢጋሮች፣ የማስተማሪያ ማቴሪያሎች ዝርዝር እና ደረጃ የወጣላቸው ፈተናዎች መርሃ ግብርን ጨምሮ፣ የጽሑፍ መግለጫ ለወላጆች/አሳዳጊዎች ይላካል። የወላጅ/አሳዳጊ እና መምህራን የቡድን ስብሰባም እንደዚሁ በበልግ ወቅት የሚካሄድ ሲሆን፣ ዓላማውም የጽሑፍ መግለጫው ላይ መወያየት፣ የዓመቱን የፕሮግራም እቅዶች ለመግለጽና የማስተማሪያ ማቴሪያሎችን ለማሳየት ነው።

መደበኛ የወላጅ/አሳዳጊ እና መምህራን ኮንፈረንሶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፦

- □ ለኮንፈረንስ ሃያ ደቂቃ እና በኮንፈረንሶች መካከል አስር ደቂቃ፤
- □ ኮንፈረንሶችን ከመደበኛው የትምህርት ሰዓት ውጭ ማካሄድ አስፈላጊ ሲሆን እንደ ሁኔታው ተለዋዋጭ መሆንና የማካካሻ ጊዜ፤ እና
- □ ለአንድ ቀን ወደ አስራ ሁለት ለሚደርሱ ኮንፈረንሶች የሚያዝ መርሃ ግብር።

ኮንፈረንሶች በመምህራን የዕቅድ ዝግጅት ጊዜ ላይ ጫና መፍጠር የለባቸውም፤ አስፈላጊ ከሆነ ተተኪዎችን መጠቀም ይገባል።

ደረጃ ላይ የተመሰረተ የእምርታ ሪፖርት በቨርጂኒያ የትምህርት ደረጃዎች (SOL) እና ለእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ በተቀመጡት በአርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች የትምህርት ተጠባቂ ውጤቶች ላይ በመመስረት ወላጆች/አሳዳጊዎች ስለተማሪዎች አካዳሚክ እምርታ መረጃ እንዲኖራቸው ያስችላል። ሪፖርቱ የመማር ስኬቶችና የእድገት እድሎችን አጉልቶ ያሳያል። ደረጃ ላይ የተመሰረቱ የእምርታ ሪፖርቶች የተለመደውን ዓይነት በፊደላት የሚገለጽ ውጤት አሰጣጥ የማይጠቀሙ ሲሆን፣ የአፈጻጸም ደረጃዎችን በመጠቀም በእያንዳንዱ የይዘት መስክ የተለዩ አበይት የትምህርት ደረጃዎች ላይ የታየ እምርታን ሪፖርት ያደርጋል። ሪፖርቱ የመምህራን አስተያየቶችንም የሚጨምር ሲሆን፣ ይህም በተለዩ ደረጃዎች ላይ የተማሪውን የብቃት ደረጃ ይበልጥ ሙሉ አድርጎ ሊያስረዳ ይችላል።

### የአርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች ደረጃ ላይ የተመሰረተ የአፈጻጸም ደረጃ ሪፖርት አደራረግ

| | |
|---|---|
| ደረጃውን ያሟላል | ተማሪው ደረጃውን የተካነ መሆኑን ወጥ በሆነ መንገድ በተግባር አሳይቷል |
| የተካነ ደረጃን ተጠግቷል | ተማሪው ደረጃውን ለመካን በሒደት ላይ ነው |
| የመካን ችሎታን በማሳደግ ላይ | ተማሪው ድጋፍ ካገኘ ስለ ደረጃው የመነሻ ግንዛቤ እንዳለው በተግባር ያሳያል |
| በቂ ያልሆነ ማስረጃ | መምህሩ አንድ ተማሪ ለደረጃ/ክህሎት ያለውን የመካን ብቃት ደረጃ ለመወሰን ማስረጃ የለውም |

### ደረጃ ላይ የተመሰረተ ሪፖርት የማድረጊያ ስርዓት ልዩ ትምህርት ውስጥ ለልዩ ማህበረሰቦች ሪፖርት ማድረግ፦

ልዩ የትምህርት አገልግሎት የሚሰጠው ተማሪ በክፍሉ ደረጃ የሚጠበቅበትን ያህል ውጤት ማምጣት ካልቻለና በደረጃ ስርዓተ ትምህርት፣ የትምህርት ዓይነት ወይም የክህሎት መስክ ላይ ከፍተኛ ማሻሻያ የሚፈልግ ከሆነ፣ ተማሪው ውጤቱ መመዘን ያለበት ከግለሰባዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ግቦች አንጻር ባስመዘገበው ስኬት መሰረት ነው። በእንደዚህ ሁኔታዎች ውስጥ ***ማሻሻያዎች*** ማለት በኮርስ፣ ደረጃ ወይም የፈተና ዝግጅት ላይ የሚደረግ ከፍተኛ ለውጥ ሲሆን፣ ለአካል ጉዳተኛ ተማሪ የተደራሽነት እድል በመፍጠር የኮርሱን፣ ደረጃውን ወይም ፈተናውን ደረጃ ወይም የክፍል ደረጃ ተጠባቂ ውጤቶች በመሰረታዊነት የሚለውጥ ወይም ዝቅ የሚያደርግ ነው።

ማሻሻያዎች ሲደረጉ በእምርታ ሪፖርቱ ላይ በሚጻፍ ማስታወሻ አማካይነት ለወላጆች/አሰዳጊዎች እንዲያውቁት ይደረጋል።

***የእንግሊዝኛ ተማሪዎች፡-*** የእንግሊዝኛ ተማሪዎች ባላቸው እምርታ መሰረት ድጋፍ የሚያገኙበት የክፍል ደረጃ ይዘት ማግኘት ይችላሉ። በእምርታ ሪፖርቱ ላይ የሚጻፉ አስተያየቶች ለእንግሊዝኛ ተማሪው የተለየ ድጋፍ የተሰጠበትን መንገድ ማመላከት አለባቸው።

***ልዩ ተሰጥኦ ያላቸው ተማሪዎች፡-*** ተገቢውን የፍጥነት አካሄድና ጥልቀት ለመድረስ ሲባል በደረጃዎች፣ የትምህርት ዓይነት ወይም የክህሎት መስኮች ላይ የሚደረጉ የስርዓተ ትምህርት ማሻሻያዎችን እነደሚያገኙ የተለዩ ተማሪዎች የሩብ ዓመት የልዩ ድጋፍ መግለጫ ሪፖርትም ይደርሳቸዋል። በቨርጂኒያ ሕግ ቁጥር 8VAC 20-40-40 ላይ እንደተደነገገው፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች የሩብ ዓመት የልዩ ድጋፍ መግለጫ ቅጾች የሚደርሳቸው ሲሆን፣ በእነዚህ ማሻሻያዎች መሰረት የተመዘገቡ የተማሪ ውጤቶች እና እድገትም ሪፖርት ይደረግላቸዋል።

## የፖሊሲ መግለጫዎች - ለወላጆች ሪፖርት ማድረግ

**ደረጃውን ለጠበቀ የሪፖርት ማድረጊያ ስርዓት ጥረት/ስራ እና ማሕበራዊ ክህሎቶች/ተሳትፎ**
ደረጃዎች ላይ የተመሰረተ የእመርታ ሪፖርት በስራ እና ማሕበራዊ ክህሎቶች ወይም C.A.R.E.S ላይም ሪፖርት ያቀርባል። C.A.R.E.S ማለት ትብብር፣ ማረጋገጫ፣ ሃላፊነት፣ ሃዘኔታና ራስን መቆጣጠር ማለት ሲሆን፣ ጥቅም ላይ የሚውለውም ምላሽ ሰጪ የመማሪያ ክፍል የመሳሰሉ ማስረጃ ተኮርና ተዋረዳዊ ማሕበራዊ/ስሜታዊ የማስተማር አቀራረብ ስርዓቶችን በሚተገብሩ ት/ቤቶች ውስጥ ነው። የስራ እና ማሕበራዊ ክህሎቶች ወይም C.A.R.E.S የተለዩ የአፈጻጸም ደረጃዎችን በመጠቀምም ሪፖርት ይደረጋሉ።

### ልማዳዊ የውጤት ሪፖርት አደራረግ K-5

የተለመደው ዓይነት ሪፖርት ካርድ በሚከተሉት መንገዶች የተማሪን እመርታ ያሳውቃል፡-

### መዋዕለ ሕጻናት

**የማርክ መስጫ ኮድ መግለጫ**
እነዚህ ምልክቶች የሚያገለግሉት አንድ ተማሪ በሚካንባቸው ክህሎቶችና ጽንሰ ሃሳቦች መሰረት እመርታውን ለማመላከት ነው፡-

| | |
|---|---|
| **M – ማሳካት** | **ተማሪው ባህሪን ወይም ክህሎትን በተከታታይ ያሳካል**<br>ተማሪው በተከታታይ ባህሪ ወይም ክህሎት ያሳካል<br>ተማሪው/ተማሪዋ ስለ ቁልፍ ጽንሰ ሃሳቦች እና ክህሎቶች በራሳቸው ግንዛቤን ያሳያሉ |
| **P – በእድገት ላይ** | **ተማሪው ባህሪ ወይም ክህሎት በማዳበር ሂደት ላይ ነው**<br>ተማሪው/ተማሪዋ ቁልፍ ክህሎቶችን፣ ስልቶችን ወይም ፅንሰ ሐሳቦችን ወጥነት በሌለው መልኩ ያሳያሉ።<br>ተማሪው/ተማሪዋ በከፊል መስፈርቱን ያሟላሉ |
| **B – ጀማሪ** | **ተማሪው ባህሪ ወይም ክህሎትን ማሳየት ጀምሯል**<br>ተማሪው ሃሳቦችን እና ችሎታዎችን መረዳት ጀምሯል እነዚህን ስራዎች ለማጠናቀቅም የመምህር እርዳታ ያስፈልገዋል። ተማሪው ሀሳቦችን እና ችሎታዎችን መረዳት ጀምሯል እነዚህን ስራዎች ለማጠናቀቅም የመምህር እርዳታ ያስፈልገዋል። |
| **N – እስካሁን ገና** | **ነው ሕጻኑ አሁንም ባህሪን ወይም ክህሎት ገና አላሳየም** |
| **NI – አልተዋወቀም** | **ክህሎት አልተዋወቀም** |

ከወላጆች/አሳዳጊዎች ጋር ግልጽ የሆነ ግንኙነት ለመመስረት፣ የቅድመ ልጅነት ጽ/ቤት ከግማሽ ዓመቱ የውጤት ሪፖርት ጋር አብረው የሚላኩ ***የአጸደ ሕፃናት አመልካች መግለጫዎችን (KIDS) ያሳትማል።*** የእመርታ ሪፖርት ጠቋሚዎች ወይም መግለጫዎች ብዙዎቹን በአጸደ ሕፃናት ውስጥ መካን የሚገቡ ክህሎቶች እና ጽንሰ-ሐሳቦችን ያንፀባርቃሉ። ለአፀደ ሕጻናት የሚሆኑ የቨርጂኒያ የትምህርት ደረጃዎች (SOL) እንደዚሁም የስራ ልማዶችና ማህበራዊ እድገት ተጠቃልለዋል።

እያንዳንዱ ልጅ በእሱ ወይም በእሷ ደረጃ የሚያድጉ እና የሚዳብሩ ግለሰቦች ናቸው። በተመሳሳይ የክፍል ደረጃ ላይ ያሉ ልጆች ከሌሎች የምድባቸው አባላት በጣም የተለዩ ሊሆኑ ይችላሉ። ***የአጸደ ሕፃናት እመርታ ሪፖርት እና የአጸደ ሕፃናት አመልካች መግለጫዎችን (KIDS)*** በትምህርት ቤት እና በቤት መካከል ግልፅ የሆነ ግንኙነት ለማቅረብ የተነደፉ ናቸው። ትምህርት ቤቶች እና ቤተሰቦች በአጋርነት አብረው በሚሰሩበት ጊዜ ልጆቻችን ትምህርት ቤት ውስጥ ለመማር እና ስኬታማ ለመሆን ጥሩ እድል ይኖራቸዋል።

## *የፖሊሲ መግለጫዎች - ለወላጆች ሪፖርት ማድረግ*

## <u>*ልማዳዊ የውጤት ሪፖርት አደራረግ* 1-5</u>

### ከአንደኛ እስከ አምስተኛ ክፍል

*አራት የጽሑፍ ሪፖርቶች በየዘጠኝ ሳምንት እንዲወጡ የጊዜ ሰሌዳ ይወጣላቸዋል። እያንዳንዱ የጽሑፍ ሪፖርት የተማሪውን ግላዊና አካዳሚክ እድገት የሚመዝንና ለመምሕራን አስተያየት መስጫ ቦታ የሚሰጥ ነው።*

*ሁለት የወላጅ/አሳዳጊ እና መምህራን ኮንፈረንሶችም የጊዜ ሰሌዳ ይወጣላቸዋል - አንዱ በበልግ ወቅት እና ሌላው በፀደይ ወቅት። የመጀመሪያው ኮንፈረንስ የሚካሄደው ት/ቤት መከፈቻ ጊዜ እና የመጀመሪያ የጽሑፍ ሪፖርት በሚዘጋጅበት ጊዜ መካከል ነው። ሁለተኛው ኮንፈረንስ የሚካሄደው ደግሞ በሁለተኛ እና ሶስተኛ የጽሑፍ ሪፖርቶች መካከል ነው።*

*የወላጅ/አሳዳጊ እና መምህራን ኮንፈረንሶች የጊዜ ሰሌዳ የሚወጣላቸው በቀጠሮ ላይ ተመስርቶ ነው። የበልግ ወቅት ኮንፈረንሶች ከመካሄዳቸው በፊት፣ ስርዓት አቀፍ የፕሮግራም ቢጋሮች፣ የማስተማሪያ ማቴሪያሎች ዝርዝር እና ደረጃ የወጣላቸው ፈተናዎች መርሃ ግብርን ጨምሮ፣ የጽሑፍ መግለጫ ለወላጆች/አሳዳጊዎች ይላካል። የወላጅ/አሳዳጊ እና መምሀራን የቡድን ስብሰባም እንደዚሁ በበልግ ወቅት የሚካሄድ ሲሆን፣ ዓላማውም የጽሑፍ መግለጫው ላይ መወያየት፣ የዓመቱን የፕሮግራም እቅዶች ለመግለጽና የማስተማሪያ ማቴሪያሎችን ለማሳየት ነው።*

*መደበኛ የወላጅ/አሳዳጊ እና መምህራን ኮንፈረንሶች የሚከተሉትን ያካትታሉ:-*

- *ለኮንፈረንስ ሃያ ደቂቃ እና በኮንፈረንሶች መካከል አስር ደቂቃ፤*
- *ኮንፈረንሶችን ከመደበኛው የትምህርት ሰዓት ውጭ ማካሄድ አስፈላጊ ሲሆን እንደ ሁኔታው ተለዋዋጭ መሆንና የማካካሻ ጊዜ፤ እና*
- *ለአንድ ቀን ወደ አስራ ሁለት ለሚደርሱ ኮንፈረንሶች የሚያዝ መርሃ ግብር።*

*ኮንፈረንሶች በመምህራን የዕቅድ ዝግጅት ጊዜ ላይ ጫና መፍጠር የለባቸውም፤ አስፈላጊ ከሆነ ተተኪዎችን መጠቀም ይገባል።*

### <u>*ልማዳዊ የውጤት ሪፖርት አደራረግ* 1-2 *ለሁሉም የይዘት መስኮች*</u>

### ከ1-2ኛ ክፍል

**P" -** *<u>የሚጠበቅበትን እመርታ እያሳያ</u> ነው ማለት የሚያመለክተው ነገር ተማሪው ካውንቲው በእያንዳንዱ የአካዳሚክ መስክ ላይ ለእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ ያስቀመጣቸውን ዓላማዎች በመረዳትና በመተግበር ረገድ ስኬታማ መሆኑን ነው።*

**"N"**-*የሚጠበቅበትን እመርታ እያሳየ አይደለም ማለት የሚያመለክተው ነገር ተማሪው ካውንቲው በእያንዳንዱ የአካዳሚክ መስክ ላይ ለእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ ያስቀመጣቸውን ዓላማዎች አለመረዳቱንና ተግባራዊም አለማድረጉን ነው።*

*ድክመት የታዩባቸው ዘርፎች (#)፣ ጥንካሬ የታዩባቸው ዘርፎች (+)፣ እና አጥጋቢ እመርታ የታዩባቸው ዘርፎች (ምልክት የለውም) በእያንዳንዱ አካዳሚክ ርዕሰ ጉዳይ ስር ለተዘረዘረው እያንዳንዱ ንኡስ ምድብ ተመላክተዋል።*

### <u>*ልማዳዊ የውጤት ሪፖርት አደራረግ ለ* 3ኛ-5ኛ ክፍል፣ ለቋንቋ ጥበባት (መጻፍና ማንበብ)፣ ሒሳብ፣ ሳይንስ፣ እና ማህበራዊ ጥናቶች</u>

## ከ3ኛ-5ኛ ክፍል

**A – በክፍል ደረጃ ከሚጠበቅበት የላቀ ውጤት**

*"A" ማለት አንድ ተማሪ በክፍሉ ደረጃ ከሚጠበቅበት ውጤት በተደጋጋሚ ልቆ ይገኛል ማለት ነው። አሳይመንቶች በትክክልና ሙሉ በሙሉ ተጠናቅቀው በወቅቱ ይመለሳሉ። አጠቃላይ አፈጻጸም እና የተማሪ ውጤቶች የላቁ ናቸው፣ ከፍተኛ መጠን ያለው ግለሰባዊ አስተሳሰብን ያንጸባርቃሉ።*

**B – በክፍል ደረጃ ከሚጠበቅበት ውጤት አብዛኛውን ጊዜ ልቆ ይገኛል**

*"B" ማለት አንድ ተማሪ በክፍል ደረጃ ከሚጠበቅበት ውጤት አብዛኛውን ጊዜ ልቆ ይገኛል ማለት ነው። አሳይመንቶች በትክክልና ሙሉ በሙሉ ተጠናቅቀው በወቅቱ ይመለሳሉ።*

**C – በክፍል ደረጃ የሚጠበቅበትን ውጤት አሳክቷል**

*"C" ማለት አንድ ተማሪ በክፍል ደረጃ የሚጠበቅበትን ውጤት አሳክቷል ማለት ነው። አሳይመንቶች በወቅቱ ይሰራሉ፣ በአጠቃላይ የተሟሉና ትክክለኛ ናቸው። የክፍል ደረጃው ዓላማዎች ተሳክተዋል።*

**D – በክፍል ደረጃ የሚጠበቅበትን ውጤት አላሳካም ማለፊያ**

"D" ማለት አንድ ተማሪ በክፍል ደረጃ የሚጠበቅበትን ውጤት አላሳካም ማለት ነው። አሳይመንቶች ብዙ ጊዜ በወቅቱ አይጠናቀቁም ምናልባትም ያልተሟሉ ወይም የተሳሳቱ ናቸው። መነሻ ዓላማዎች ተሳክተዋል። የስራው ደረጃ ወደ ቀጣይ ክፍል ለመዛወር ተቀባይነት የሚኖረው ዝቅተኛው መጠን ነው።

**E – በክፍል ደረጃ የሚጠበቅበትን ውጤት አላሳካም ዝቅተኛ**

"E" ማለት አንድ ተማሪ በክፍል ደረጃ የሚጠበቅበትን ውጤት አላሳካም ማለት ነው። የ የስራው ደረጃ አጥጋቢ አይደለም። "E ስራው ወደ ቀጣይ ክፍል ለመዛወር ተቀባይነት የለውም።

## የፖሊሲ መግለጫዎች - ለወላጆች ሪፖርት ማድረግ

**ለ3ኛ-5ኛ ክፍሎች በሙዚቃ፣ የሰውነት ማጎልመሻ እና አርት ትምህርቶች የሚመዘገብ ስኬት**

በሙዚቃ፣ የሰውነት ማጎልመሻ እና አርት የትምህርት መስኮች፣ ውጤት ሪፖርት የሚደረገው ቀጣዮቹን ምልከቶች በመጠቀም ነው:-

**B – በጅምር ላይ ያለ:-** ተማሪው የትምህርት ይዘት ማቴሪያሉ ተገልጾለታል።

**P – በመሻሻል ላይ ያለ:-** ተማሪው በአሁኑ ጊዜ ክህሎቶችች እና የትምህርት ይዘት ማቴሪሎችን ግንዛቤ እያሳደገ ነው።

**S – ክህሎት ያለው:-** ተማሪው ስለ ትክክለኛ አተገባበር ክህሎትን በተግባር ያሳየና የትምህርት ይዘት ማቴሪያሉን መቼ እና እንዴት መተግበር እንዳለበት ግንዛቤ ያለው ነው።

**O – የላቀ:-** ተማሪው የላቀ ቢቃትና ግንዛቤን በተግባር አሳይቷል፣ የተማራቸውን ደረጃዎች አውቆ እነርሱንም ልቆ ሄዷል።

**ለ1ኛ-5ኛ ክፍሎች ልማዳዊ ሪፖርት አደራረግ ስርዓት ጥረት/ስራ እና ማሕበራዊ ክህሎቶች/ተሳትፎ**

ውጤት ከማስመዝገብ በተጨማሪ፣ ተማሪው በእያንዳንዱ የአካዳሚክ መስክ የሚያደርገው ጥረት፣ በተወሰኑ ልዩ የትምህርት ዓይነቶች ላይ ያስመዘገበው ውጤት፣ የስራ ልማዶች እና ማሕበራዊ ክህሎቶች ተገምግመው ውጤታቸው የሚገለጸው በሚከተሉት ምልክቶች ነው:-

**O – የላቀ**

**S – አጥጋቢ**

**I- እያሻሻለ ነው**

**N- ማሻሻል ይገባዋል**

**የልዩ ፍላጎት ትምህርት:-** የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎት የሚያገኝ ተማሪ ለክፍል ደረጃው የሚጠበቅበትን ውጤት ማስመዝገብ ካልቻለና መደበኛው ስርዓት ትምህርት፣ የትምህርት ዓይነት ወይም የክህሎት መስክ ላይ ከፍተኛ የሆነ ማሻሻያ ካስፈለገው፣ ውጤት ሊሰጠው የሚገባው በተገለጸው የ IEP ግቦች ስኬት ላይ ተመስርቶ ነው።

በእንደዚህ ሁኔታዎች ውስጥ ማሻሻያዎች ማለት በኮርስ፣ ደረጃ ወይም የፈተና ዝግጅት ላይ የሚደረግ ከፍተኛ ለውጥ ሲሆን፣ ለአካል ጉዳተኛ ተማሪ የተደራሽነት እድል በመፍጠር የኮርሱን፣ ደረጃውን ወይም ፈተናውን ደረጃ ወይም የክፍል ደረጃ ተጠባቂ ውጤቶች በመሰረታዊነት የሚለውጥ ወይም ዝቅ የሚያደርግ ነው። ከአንድ ውጤት አጠገብ የኮከብ (*) ምልክት መኖሩ የሚያመለክተው የማሻሻያዎችን አጠቃቀም ሆኖ ወላጆች/አሳዳጊዎች ማብራሪያ ወደሚሰጥበት የገለጻ ክፍል እንዲሄዱ የሚመራ ነው። ተማሪው ስርዓተ ትምህርቱን ለመድረስ የሚያግዘው ምቹ ሁኔታ እያገኘ ከሆነ (*) መጠቀም አያስፈልግም። የኮከብ ምልክቱን መጠቀም ያለብን በመደበኛ ስርዓት ትምህርት፣ የትምህርት ዓይነት ወይም የክህሎት መስክ ላይ ከፍተኛ የሆነ ማሻሻያዎች የተደረጉ ከሆነ ብቻ ነው።

## የፖሊሲ መግለጫዎች - ለወላጆች ሪፖርት ማድረግ

**የእንግሊዝኛ ተማሪዎች፡-** የእንግሊዝኛ ተማሪዎች የመምህራን ድጋፍ የሚሰጥባቸው የክፍል ደረጃ ይዘት ማግኘት ይችላሉ። ከአንድ የተሰጠ ውጤት አጠገብ የካሮት ምልክት (^) መጠቀም የሚያመለክተው ተጨማሪ አስተያየት (በሪፖርት ካርዱ ላይ የሚጻፍ ተጨማሪ አስተያየት) መኖሩን ሲሆን፣ ለእንግሊዝኛ ተማሪው የተሰጠው ልዩ ድጋፍ የሚብራራበት ቦታ ነው።

**ልዩ ተሰጥኦ ያላቸው ተማሪዎች፡-** ከሌሎች ተማሪዎች ጋር እንዲመጣጠኑና አቅም እንዲያሳድጉ ሲባል በስታንዳርድ፣ የትምህርት ዓይነት ወይም የክህሎት መስኮች ላይ የስርዓተ ትምህርት ማሻሻያዎች ይደረግላቸዋል ተብለው የተለዩ ተማሪዎች በየሩብ ዓመቱ የሚቀርብ የልዩ ድጋፍ ሪፖርትም ይደርሳቸዋል። በቨርጂኒያ ሕገ ደንብ 8VAC 20-40-40 ላይ እንደተገለጸው፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች በየሩብ ዓመቱ የልዩ ድጋፍ ቅጾች የሚደርሳቸው ሲሆን፣ በእነዚህ ማሻሻያዎች ላይ ተመስርቶ የተማሪ ውጤቶችና እድገት ሪፖርት ይደረግላቸዋል።

## <u>አማራጭ የእመርታ ሪፖርቶች</u>

<u>የተሻሻለ የእመርታ ሪፖርት</u>

አንዳንድ ተማሪዎች በልዩ ፍላጎት ፕሮግራሞች ውስጥ የሚመዘገቡ ሲሆን፣ በዚህ ምክንያት መደበኛው የእመርታ ሪፖርት አግባብነት አይኖረውም። ከእነዚህ ተማሪዎች መካከል አብዛኞቹ የአካል ጉዳት ያለባቸውና የልዩ ፍላጎት ትምህርት እና/ወይም ተዛማጅ አገልግሎቶችን የሚያገኙ ናቸው። እያንዳንዱ የተለየ አካል ጉዳተኛ ተማሪ በት/ቤት ሰራተኞች፣ በወላጆች እና እንዳግባብነቱም በተማሪው የሚዘጋጅ ግለሰባዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) አለው። IEP ከፍላጎቶች ጋር የሚዛመዱ ውስን ግቦችና ዓላማዎችን ያካትታል።

አካል ጉዳተኛ መሆናቸው የተለየና የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶችን የሚያገኙ ተማሪዎች ከልዩ ፍላጎት ትምህርት መምህሩ የእመርታ ሪፖርት ማግኘት አለባቸው፤ ሪፖርቱ የሚሰጥበት የጊዜ ድግግሞሽ ከመደበኛ ትምህርት የጽሁፍ ሪፖርቶች ጋር ተመሳሳይ ነው። እነዚህ ሪፖርቶች ከመደበኛው የትምህርት እመርታ ሪፖርት ተጨማሪ ሆነው፣ የ IEP ግቦች ላይ የታየ እመርታንም ማካተት አለባቸው።

የልዩ ፍላጎት ትምህርት መምህራንም መደበኛ የጊዜ ሰሌዳ በሚወጣለት የወላጆችና መምህራን ኮንፈረንስ ላይ ይሳተፋሉ። ሌላ ከዚህ የተለየ ሪፖርት የማድረግ አሰራር <u>ደረጃውን ያልጠበቀ</u> ሪፖርት ተደርጎ የሚቆጠር ሲሆን በዚህ መምሪያ ውስጥ በተዘረዘሩት አሰራሮች መሰረት ነው መዘጋጀት ያለበት።

በመደበኛው ፕሮግራም ውስጥ እየተማሩ ላሉና በልዩ ሁኔታዎች ምክንያት ዓመቱን ሙሉ ዝቅተኛ ውጤት ሊያስመዘግቡ ለሚችሉ ተማሪዎች የሐተታ መግለጫ ሪፖርትን መጠቀም ይቻላል። መምህራን፣ ወላጆችና ርዕሰ መምህሩ የሐተታ መግለጫ ሪፖርቱን በመደበኛ የእመርታ ሪፖርት የመተካት ውሳኔ ውስጥ ይሳተፋሉ። የሐተታ መግለጫ ሪፖርቱ ተማሪዎች በንባብ፣ ሒሳብ እና ቃላት ላይ ያላቸውን የማስተማር ደረጃ የሚያካትት ሲሆን፣ ተማሪው ወደ ቀጣይ ክፍል ከመዛወሩ ወይም ከመድገሙ ጋር በተያያዘ ያለውን ሁኔታ ያመለክታል።

***<u>መደበኛ ያልሆነ ሪፖርት</u>***

አግባብነት ያለው ምክንያት ሲኖር፣ እያንዳንዱ የት/ቤት ማህበረሰብ የተፈቀደ አሰራርን ተጠቅሞ ከመደበኛው ሪፖርት የማድረጊያ ስርዓት የተለየ ሪፖርት የማድረጊያ ስርዓትን አዘጋጅቶ ሊጠቀም ይችላል። መደበኛ ያልሆነ ሪፖርትን አስፈላጊ ከሚያደርጉት ምክንያቶች መካከል የአዳዲስ ፈጠራ ፕሮግራሞች፣ ያልተለመዱ ስነ-ሕዝባዊ ጉዳዮች እና/ወይም ልዩ የተግባቦት ፍላጎቶች ይገኙበታል። መደበኛ ያልሆነ ሪፖርት ከማዛወር እና ከማስደገም ፖሊሲዎች ጋር መጣጣም አለበት።

ለመደበኛው ሪፖርት አጋዥ የሆነ ሪፖርት የማድረጊያ መረጃ በእያንዳንዱ ት/ቤት ውሳኔ መሰረት ሊታከል ይችላል፣ መደበኛ ያልሆነ ሪፖርት የማጽደቂያ አሰራሮችንም አይከተልም።

ከአንድ የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ጋር ግንኙነት ያላቸው ፕሮፌሽናል ሰራተኞች ወይም ማህበረሰብ በሪፖርት ማድረጊያ ስርዓቱ ላይ ለውጥ እንዲደረግ በቀጣዩ መንገድ ምክረ ሃሳብ ሊሰጥ ይችላል።

1. መደበኛ ያልሆነ ሪፖርት ማድረጊያ ስርዓት ፕሮፖዛሎች በት/ቤቱ ሰራተኞችና የለውጡ ሃሳብ አመንጪ የሆነው የት/ቤት ማህበረሰብ ተወካይ ሊጠና ይችላል። ፕሮፖዛሎች ወደ ማዕከላዊ ቢሮ ከመላካቸው በፊት ለወላጅ/መምህራን ማህበር ቀርበው መፅደቅ አለባቸው።

2. ፕሮፖዛሎች በጽሑፍ ተዘጋጅተው ለቺፍ አካዳሚክ ኦፊሰር ቀርበው ለሱፐርኢንቴንደንት ምክረ ሃሳብ ይሰጥባቸዋል።



3. ሱፐርኢንቴንደንት የመጨረሻውን ምክረ ሃሳብ ለት/ቤት ቦርድ አቅርበው ያስጸድቃሉ። መደበኛ ያልሆኑ የእመርታ ሪፖርቶች ፕሮፖዛሎች በየዓመቱ መቅረብ አለባቸው።

# የፖሊሲ መግለጫዎች - ወደ ቀጣይ ክፍል መዛወር እና ክፍል መድገም

**ወደ ቀጣይ ክፍል መዛወር**

ወደ ቀጣይ ክፍል መዛወር የሚመሰረተው አንድ ግለሰብ በአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ ለእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ ከተቀመጡ ዓላማዎች ጋር የተያያዙ ክህሎቶችን እውቀት እና የስራ ልማዶችን መቅሰሙ ላይ ነው።

ከአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ጀምሮ የሚኖር እመርታ ከላይ በተገለጸው ፖሊሲ ውስጥ የተቀመጠውን አጠቃላይ አካሄድ ይከተላል። ከአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ወደ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ዝውውር የሚደረገው ከአጸደ ሕጻናት እስከ 5ኛ ክፍል ድረስ በተለመደ መልኩ እመርታ ከተመዘገበ በኋላ ነው። ይሁን እንጂ፣ ግለሰባዊ ልዩነቶች ከዚህ ልማድ ማፈንገጥን ሊጠይቁ ይችላሉ፤ በአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ የተፋጠነ ወይም የዘገዬ እንቅስቃሴ የሚደረገው በተመለከተው መንገድ ነው።

በየትኛውም ሁኔታ ቢሆን፣ የልጁ ወላጆች ማፋጠን ወይም ማስደገምን የሚያስከትለው እቅድ ዝግጅት ውስጥ ተሳታፊ ናቸው። ታሳቢ መደረግ ካለባቸው ጉዳዮች መካከል ተማሪው በክፍል ውስጥ ብቃቱ የሚያስመዘግበው ውጤት፣ የመምህሩ ሕሊናዊ ፍርድ፣ የስኬት ፈተናዎችና በእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ ከተቀመጡ ዓላማዎች ጋር በተያያዘ መስፈርት ጠቀስ እርምጃዎች ይገኙበታል።

**ክፍል መድገም**

አንድ ተማሪ በሚማርመበት የክፍል ደረጃ እንዲደግም የሚደረገው የትምህርት ዕድገቱ ወደ ቀጣዩ የክፍል ደረጃ እንዲዛወር የማያበቃው ሲሆን ነው። ክፍል ማስደገም በእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ ከተቀመጡት ዓላማዎች ጋር በተያያዘ በአካዳሚክ ብቃት ላይ የተመሰረተ ነው።

**ክፍል የማስደገም ውሳኔ**

የት/ቤቱ ሰራተኞች አንድ ተማሪ ባለበት ክፍል እንዲደግም ምክረ ሃሳብ የሚሰጡት ውሳኔው የተማሪውን ዘላቂ ስኬት የሚጠቅም ሲሆን ነው። ታሳቢ ከሚደረጉ ጉዳዮች መካከል፦

- በመሰረታዊ የንባብ፣ መጻፍ እና ሒሳብ ክህሎቶች ላይ በክፍል ውስጥ የሚኖር ብቃት በሪፖርት ካርድ፣ በስኬት ፈተናዎች እና መስፈርትን በሚያጣቅሱ እርምጃዎች መሰረት።
- በእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ ከተቀመጡ ዓላማዎች አንጻር ተማሪው ያስመዘገበውን ውጤት በተመለከተ የመምህሩ ሕሊናዊ ፍርድ።
- ክፍል ከመድገም፣ በመሰረታዊ የክህሎት መስኮች ከሚሰጥ ማካካሻ እና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት ጋር በተያያዘ ተማሪው የነበረው ልምድ።

**ወላጆችን ማማከር**

አንድን ተማሪ ክፍል ለማስደገም ሲታሰብ፣ የተማሪው ወላጆች በፀደይ ወቅት ከሚካሄደው የወላጆችና መምህራን ኮንፈረንስ በኋላ ጀምሮ በቅድሚያ የእቅድ ዝግጅት ላይ ይሳተፋሉ። በትምህርት ዘመኑ ዘግይተው የሚመጡ ተማሪዎችን ለማዛወር ሲባል በዚህ ውስጥ የማይካተቱ ልዩ ሁኔታዎች ሊያስፈልጉ ይችላሉ። ክፍል ማስደገም የሚመከር ከሆነ፣ ወላጆች እንዲያውቁት ተደርጎ ክፍል የሚደገምበት ምክንያት ላይ ውይይት ይደረጋል። አሳይመንትን በተመለከተ የመጨረሻው ሃላፊነት የርዕስ መምህሩ ይሆናል።

## ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች

አርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች በመላው 26 የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ውስጥ የተለያዩ ፕሮግራሞችና አገልግሎቶችን ያቀርባል። ሁሉም የአርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች ከቨርጂኒያ ግዛት የትምህርት ቦርድ ከደቡባዊ የኮሌጆችና ት/ቤቶች ማህበር የእውቅና ፈቃድ ተሰጥቷቸዋል። ቨርጂኒያ ውስጥ ለሚገኙ ት/ቤቶች የእውቅና ፈቃድ መስጫ መስፈርቶች ጥራት ላለው ትምህርት መሰረት ለመጣል ተብለው የተቀረጹ ናቸው። እነዚህ መስፈርቶች ት/ቤቶች የሁሉንም ተማሪዎች ፍላጎቶች፣ ጥቅሞችና የወደፊት ምኞቶች የሚያሳኩ ትምህርታዊ ፕሮግራሞችን ለማቅረብ በሚያደርጓቸው ቀጣይነት ያላቸው ጥረቶች ላይ የሚያግዙ አመራርና አቅጣጫን ይሰጣሉ።

በቀጣዩ ክፍል፣ የእያንዳንዱ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ዝርዝር እና በመላው ካውንቲ እንደዚሁም በእያንዳንዱ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ የሚሰጡ ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች መግለጫን ያገኛሉ። የአጎራባች አካባቢና የካውንቲ አቀፍ ት/ቤቶች አማራጮችን የተመለከተ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት፡- የምዝገባ መምሪያ መፅሐፍ ለወላጆች ከዚህ ያገኛሉ፡- http://apsva.us/publications/. ተጨማሪ መረጃ ከአርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች ድረ ገጽ ላይም ማግኘት ይቻላል።

**Abingdon Elementary**
David Horak፣ ርዕሰ መምህር
Anne Oliveira and Michele Micael፣ ረዳት ርዕሰ መምህራን
3035 S. Abingdon Street, 22206
703-228-6650
https://abingdon.apsva.us

**Arlington Science Focus School**
Mary Begley፣ ርዕሰ መምህር
Barbara Jones፣ ረዳት ርዕሰ መምህር
1501 N. Lincoln Street, 22201
703- 228-7670
https://asfs.apsva.us

**Arlington Traditional School**
Sam Podbelski፣ ርዕሰ መምህር
Inga Schoenbrun፣ ረዳት ርዕሰ መምህር
1030 N. McKinley Road, 22205
703- 228-6290
https://ats.apsva.us

**Ashlawn Elementary**
Frances Lee፣ ርዕሰ መምህር
Meghan Neary፣ ረዳት ርዕሰ መምህር
5950 North 8th Road, 22205
703- 228- 6650
https://ashlawn.apsva.us

**Barcroft Elementary**
Judy Apostolico-Buck፣ ርዕሰ መምህር
Gabriela Rivas፣ ረዳት ርዕሰ መምህር
625 Wakefield Street, 22204
703- 228-5838
https://barcroft.apsva.us

**Barrett Elementary**
Catherine Han፣ ርዕሰ መምህር
Amin Littman፣ ረዳት ርዕሰ መምህር
4401 North Henderson Road, 22203
703- 228-6288
https://barrett.apsva.us

**Campbell Elementary**
Maureen Nesselrode፣ ርዕሰ መምህር
Karen Anselmo፣ ረዳት ርዕሰ መምህር
737 S. Carlin Springs Road, 22204
703- 228- 6770
https://campbell.apsva.us

**Cardinal Elementary**
Colin Brown፣ ርዕሰ መምህር
Gina Miller፣ ረዳት ርዕሰ መምህር
1644 N. McKinley Road, 22205
703- 228-5280
https://cardinal.apsva.us

**Carlin Springs Elementary**
ዶ/ር Melaney Mackin፣ ርዕሰ መምህር
Marcelo Flores፣ ረዳት ርዕሰ መምህር
5995 South 5th Roade, 22204
703- 228-6645
https://carlinsprings.apsva.us

**Claremont Elementary**
Jessica Panfil፣ ርዕሰ መምህር
Erin Wales-Smith፣ ረዳት ርዕሰ መምህር
4700 S. Chesterfield Road, 22206
703- 228-2685
https://claremont.apsva.us

**Discovery Elementary**
Erin Russo፣ ርዕሰ መምህር
ዶ/ር Judith Seeber፣ ረዳት ርዕሰ መምህር
5241 N. 36th Street, 22207
703- 228-2685
https://discovery.apsva.us

**Drew Elementary**
Tracy Gaither፣ ርዕሰ መምህር
James Welch፣ ረዳት ርዕሰ መምህር
3500 S. 24th Street, 22206
703- 228-5825
https://drew.apsva.us

**Fleet Elementary**

**Glebe Elementary**

Jennifer Gildea፣ ርዕሰ መምህር
Rebecca Ward፣ ረዳት ርዕሰ መምህር
115 South Old Glebe Road, 22204
703- 228-5820
https://fleet.apsva.us

**Hoffman-Boston Elementary**
Heidi Smith፣ ርዕሰ መምህር
Suzanne Paul፣ ረዳት ርዕሰ መምህር
1415 S. Queen Street, 22204
703- 228-5845
https://hoffmanboston.apsva.us

**Jamestown Elementary**
Michelle McCarthy፣ ርዕሰ መምህር
ዶ/ር Monica Roaché፣ ረዳት ርዕሰ መምህር
3700 N. Delaware Street, 22207
703- 228-5275
https://jamestown.apsva.us

**Long Branch Elementary**
Jessica DaSilva፣ ርዕሰ መምህር
Carolyn Jackson፣ ረዳት ርዕሰ መምህር
33 N. Fillmore Street, 22201
703- 228-4220
https://longbranch.apsva.us

**Nottingham Elementary**
ዶ/ር Eileen Gardner፣ ርዕሰ መምህር
ዶ/ር Megan Lynch፣ ረዳት ርዕሰ መምህር
5900 Little Falls Road, 22207
703- 228-5290
https://nottingham.apsva.us

**Randolph Elementary**
Carlos Ramirez፣ ርዕሰ መምህር
Jennifer Denino፣ ረዳት ርዕሰ መምህር
1306 S. Quincy Street, 22204
703- 228-5830
https://randolph.apsva.us

**Tuckahoe Elementary**
Dustin Barnes፣ ርዕሰ መምህር
Michele Maurer፣ ረዳት ርዕሰ መምህር
6550 N. 26th Street, 22213
703- 228-5288
https://tuckahoe.apsva.us

Jaime Lee Borg፣ ርዕሰ መምህር
Ingrid Clark-Marshall፣ ረዳት ርዕሰ መምህር
1770 N. Glebe Road, 22207
703- 228-6280
https://glebe.apsva.us

**Innovation Elementary**
Claire Peters፣ ርዕሰ መምህር
Kathryn White፣ ረዳት ርዕሰ መምህር
2300 Key Blvd, 22201
703- 228-2700
https://innovation.apsva.us

**Key School- Escuela Key**
Marleny Perdomo፣ ርዕሰ መምህር
Erika Sanchez፣ ረዳት ርዕሰ መምህር
855 North Edison Street, 22205
703- 228-8495
https://key.apsva.us

**Montessori Public School of Arlington**
Catarina Genove፣ ርዕሰ መምህር
Yolanda Nashid፣ ረዳት ርዕሰ መምህር
701 S. Highland Street, 22204
703- 228-8871
https://montessori.apsva.us

**Oakridge Elementary**
ዶ/ር Lynn Wright፣ ርዕሰ መምህር
Laurel Cerrud፣ ረዳት ርዕሰ መምህር
1414 S. 24th Street, 22202
703- 228-5840
https://oakridge.apsva.us

**Taylor Elementary**
Katie Madigan፣ ርዕሰ መምህር
Caitlin Sherman፣ ረዳት ርዕሰ መምህር
2600 N. Stuart Street, 22207
703- 228-6275
https://taylor.apsva.us

**ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች**

አርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች የተለያዩ ፕሮግራሞችና አገልግሎቶችን ያቀርባል። የተመረጡ ቢሮዎች የግንኙነት መረጃ ከታች ተዘርዝሯል።

**የስነ ጥበብ ትምህርት**
ዶ/ር Pam Farrell፣ ተቆጣጣሪ
703-228-6170

**ሙያ፣ ቴክኒካዊ እና የጎልማሶች ትምህርት**
Kris Martini፣ ዳይሬክተር
703-228-7029

**ስርዓተ ትምህርት እና ትምህርት አሰጣጥ**
Sarah Putnam, ዋና ዳይሬክተር
Kerri Hirsch, Director
703-228-2879

**የቅድመ ልጅነት ትምህርት**
Elaine Perkins፣ አስተባባሪ
703-228-8632

**የት/ቤት ድጋፍ አንደኛ ደረጃ ጽ/ቤት**
Wendy Pilch፣ ዳይሬክተር
703-228-8632

**የእንግሊዝኛ ቋንቋ ጥበባት**
Sarah Cruz, Elementary ተቆጣጣሪ
703-228-8045

**የሚዛናዊነትና ልህቀት ጽ/ቤት**
ዶ/ር Jason Ottley፣ መሪ
703- 228-6156

**የእንግሊዝኛ ተማሪዎች**
Terri Murphy፣ ዳይሬክተር
703-228-6095

**ከት/ቤት ሰዓት በፊትና በኋላ የሚጨመር ጊዜ**
Robert Kaplow, Director
703-228-6068

**የፌዴራል ፕሮግራሞች አስተባባሪ**
Cate Coburn፣ አስተባባሪ
703-228-6161

**የተሰጥኦ አገልግሎቶች**
Cheryl McCullough፣ ተቆጣጣሪ
703-228-6160

**የጤና እና ሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት**
Deborah DeFranco፣ ተቆጣጣሪ
703-228-6165

**የቋንቋ አገልግሎቶች፣**
**የምዝገባ እና የእንግዶች መቀበያ ማዕከል**
Jeff Lash፣ አስተባባሪ
703-228-7663

**የቤተ-መጻሕፍት አገልግሎቶች**
Amy Hailey፣ ተቆጣጣሪ
703-228-6085

**ሒሳብ**
Shannan Ellis, Elementary ተቆጣጣሪ
703-228-6135

**ሳይንስ**
ዶ/ር Dat Le፣ ተቆጣጣሪ
703-228-6166

**ማህበራዊ ጥናቶች**
Terrell Fleming፣ ተቆጣጣሪ
703-228-6140

**የተማሪ አገልግሎቶች**
ዶ/ር Darrell Sampson፣ ዋና ዳይሬክተር
703-228-6058

**የልዩ ፍላጎት ትምህርት**
ዶ/ር Kelly Krug, Elementary ዳይሬክተር
703-228-6040

**የዓለም ቋንቋዎች**
Elisabeth Harrington፣ ተቆጣጣሪ
703-228-6097

# ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች

## *የእንግሊዝኛ ተማሪዎች አገልግሎቶች*

የእነግሊዝኛ ተማሪ አገልግሎቶች ከአፀደ ሕጻናት እስከ አምስተኛ ክፍል ላሉ ለተለዩ ተማሪዎች በአካዳሚክ ይዘት እና ቋንቋ ላይ ትምህርታዊ ድጋፍ ይሰጣሉ። ተማሪዎች በእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታቸው (ELP) ላይ በመመስረት በየዓመቱ ተመዝነው ከአምስቱ ደረጃዎች (1ኛ-4ኛ ወይም ደረጃ 6) በአንዱ ላይ ይመደባሉ። የELP ደረጃቸው 1፣ 2 እና 3 የሆኑ ተማሪዎች የቋንቋ ብቃታቸው አዲስ ገቢ፣ ጀማሪ እና መካከለኛ ነው። በደረጃ 4 ላይ የተመደቡ ተማሪዎች የቋንቋ ብቃታቸው የላቀ ነው። የእንግሊዝኛ ተማሪ አገልግሎቶች ደረጃ 6 የደረሱ የተባሉና የላቀ ብቃት ያላቸው ተማሪዎችን እመርታ የሚደግፍና የሚከታተል ነው።

በደረጃ 1-4 ላይ የተመደቡ ተማሪዎች በየዓመቱ አንብቦ መረዳትና ተግባቦትን በግዛት ከስቴት የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች (ACCESS for ELLs) የቋንቋ ብቃት ፈተና እና የአካባቢ ምዝናዎች አማካይነት ይመዘናሉ። በACCESS for ELLs መሰረት፣ ተማሪዎች ደረጃ 6 ላይ ሲደርሱ፣ የእንግሊዝኛ ብቃታቸው የላቀ ሲሆን የእንግሊዝኛ ተማሪ አገልግሎቶችን አያገኙም።

ለተጨማሪ መረጃ፣ እባክዎ መምህር(መምህራን)ዎን ያናግሩ ወይም ቀጣዩን የእንግሊዝኛ ተማሪዎች ድረ ገጽ ይጎብኙ፡- https://www.apsva.us/english-learners/።

## *አርአያ የሚሆኑ ፕሮጀክት*

አርአያ የሚሆኑ ፕሮጀክቶች የሚቀረጹት አዳዲስ የማስተማሪያ ሞዴሎችን በመጠቀም የተማሪ ትምህርትን ለማሻሻልና የአካዳሚክ ስኬት ውጤትን ለማጎልበት፤ በት/ቤት ላይ ፍላጎትን ለማሳደግ፤ እና በት/ቤት ውስጥ የማስተማር ትስስርን ለማጠናከር ነው። እያንዳንዱ አርአያ የሚሆን ፕሮጀክት፡-

- በት/ቤቱ ውስጥ ለተመዘገቡ ሁሉም ተማሪዎች ትምህርትን ማጎልበት
- የት/ቤት የማስተማሪያ ውህደትን ማጠናከር
- የአካባቢው ማህበረሰብ ለት/ቤት ያለውን ቁርጠኝነት ማገንባት
- ግልጽ የሆነ የግምገማ እቅድ እና ሪፖርት ማድረጊያ የጊዜ ሰሌዳ ማካተት አለበት

አርአያ የሚሆኑ ፕሮጀክቶች በት/ቤቱ ማህበረሰ የተገለጹትን ውስን የተማሪዎችን ፍላጎቶችና ውጤቶች የሚያንጸባርቁ ሲሆን፣ የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፡-

- በተወሰኑ የማስተማሪያ ዘዴዎች ላይ ለሰራተኞች የሚሰጥ ሙያዊ ማጎልበቻ
- ተጨማሪ ሰራተኞች እና/ወይም የፕሮጀክት አስተባባሪ
- ልዩ የማስተማሪያ ማቴሪያሎች ያላቸው የተለዩ የማስተማሪያ ቦታዎች
- የበለጸገ ስርዓተ ትምህርት
- ከቢዝነሶች እና የማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር የሚፈጠር አጋርነት
- የት/ቤት እንቅስቃሴዎችና ከቤተሰቦች ጋር የሚደረግ ተግባቦት መጨመር

አርአያ የሚሆኑ ፕሮጀክቶች የ APS ስትራቴጂክ እቅድ ትምህርታዊ ዓላማዎችን እያሳኩ ት/ቤቶች ለየት ያለ ማንነት እንዲፈጥሩ ያግዛሉ። አርአያ የሚሆኑ ፕሮጀክቶች ለአጠቃላዩ የት/ቤት ማሕበረሰብ ተጠሪ በመመደብ ትኩረትን ወደ ጋራ ግቦች በመምራት ለተማሪዎች፣ ቤተሰቦችና ሰራተኞች ተነሳሽነትን ይፈጥራሉ፤

# ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች

**<u>የሂውማኒቲስ ፕሮጀክት 703-228-6299</u>**

በስነ ጥበብ ትምህርት ቢሮ የሚመራው የአርቲስት በትምህርት ፕሮግራም የሆነው የሂውማኒቲስ ፕሮጀክት ትእይንቶችን፣ ተቀማጭ ተማሪዎችና ወርክሾፖችን ስፖንሰር ያደርጋል። በእያንዳንዱ የአርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤት ውስጥ፣ በሁሉም የክፍል ደረጃ ላይ የሚገኙ ተማሪዎች በየዓመቱ በተጋባዥ አርቲስቶች ይጎበኛሉ። የሂውማኒቲስ ፕሮጀክት የት/ቤቶችና ማህበረሰቡን የተቀናጀ ሐብት በመጠቀም ትምህርትን በስነ ጥበብ በኩል ያሳድጋል። የላቀ ጥበባዊ ጥራት ያላቸውና ጥበብን ከሌሎች የአካዳሚክ ዘርፎች ጋር የሚያቀናጁ ፕሮግራሞች በሂውማኒቲስ ፕሮጀክት ውስጥ እንዲሳተፉ ተመርጠዋል። የፕሮግራሞች ዳይሬክተሪ በስነ ጥበብ ትምህርት ጽ/ቤት ይገኛል።

**<u>ጁኒዬር ኦነርስ የሙዚቃ ፕሮግራሞች 703-228-6171</u>**

ጁኒየር ኦነርስ የሙዚቃ ፕሮግራም የአንደኛ ደረጃ የክብር ሕብረ ዘማሪያን (5ኛ ክፍል)፣ ጁኒዬር የክብር ባንድ (4ኛ- 6ኛ ክፍል) እና ጁኒዬር የክብር ኦርኬስትራ (4ኛ-6ኛ ክፍል) ያካተተ ነው። ጁኒዬር ኦነርስ ፕሮግራሞች በስነ ጥበብ ትምህርት ጽ/ቤት የሚተዳደሩ ናቸው። እነዚህ የሙዚቃ ፕሮግራሞች የተቀረጹት በስነ ጥበብ ላይ ልህቀትን ለማበረታታትና ከፍተኛ ተነሳሽነት ላላቸው እና/ችሎታ ላላቸው ተማሪዎች የሙዚቃ ተሞክሮዎችን ለማቅረብ ነው። የእነዚህ ፕሮግራሞች የመመዘኛ ፈተናዎች በበልግ ወቅት የሚካሄዱ ሲሆን በት/ቤቱ የሙዚቃ ሰራተኞች እና በ APS ድረ ገጽ በኩል የሚተዋወቁ ይሆናል። ልምምዶች በክረምት ወቅት እስከ 14 ሳምንት ድረስ ይወስዳሉ፣ በፀደይ ወቅት መግቢያ ላይ ደግሞ ኮንሰርት ይዘጋጃል።

**<u>የቤተ መጻሕፍት አገልግሎቶች 703-228-6085</u>**

ቤተ መጻሕፍቱ ለመማርና ራሱን ለቻለ ንባብ የሚሆኑ የሕትመትና ዲጂታል የመረጃ ምንጮችን በማዘጋጀት የሁሉንም ተማሪዎች አእምሯዊ፣ ስሜታዊና ማህበራዊ ዕድገትን ያጎለብታል። ተማሪዎች የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የመጨረሻ ተጠቃሚ እና የእድሜ ልክ ተማሪዎች ይሆኑ ዘንድ የ21ኛ ክፍለ ዘመን ክህሎቶችን ይማራሉ። ቤተ መጻሕፍቱ ወቅቱን የጠበቀ የመጽሐፍ ስብስብ ያለው ሲሆን ይህን ስብስብ በቦታውና ከቦታው ውጭ ማግኘት ይቻላል፣ የጉዳዩን ይዘት፣ የማንልበቻ ፍላጎቶች፣ ሰፊ እይታዎችና የባሕል እና የብሔር ብዝሃነትን ከግምት ውስጥ ያስገባል።

የት/ቤት ቤተ መጽሐፍት ባለሙያዎች ተማሪዎች በአሳይመንቶቻቸው ውስጥ መረጃን እንዲጠቀሙና እንዲያቀናጁ መመሪያ ይሰጣሉ። ተማሪዎች መረጃን መልሶ ለማግኘት፣ ለማደራጀት፣ ለመሰነድ፣ ለመተንተን፣ ለመገምገም፣ ለመዘርዘርና ለማቅረብ የቤተ መጻሕፍት ማቴሪያሎችን በተለያዩ ቅርጸቶች ይጠቀማሉ። ተማሪዎች መረጃን በአግባቡ ለመጠቀም ተቀባይነት ያላቸው ፖሊሲዎችን እንዲያከብሩም ይማራሉ። የቤተ መጽሐፍት ባለሙያዎችም ከመምህራን ጋር በመተባበር የስርዓተ ትምህርት ክፍሎችን ይገነባሉ፣ ልዩ ፕሮግራሞችና ከመደበኛው ሰዓት በላይ በመምራት ተማሪዎችና ሰፊው የት/ቤት ማሕበረሰብ የንባብ እድሎቹን ለማሳደግ ያስችሉታል።

ተማሪዎችና ቤተሰቦቻቸው የቤተ መጻሕፍቱን ግብዓቶች ከት/ቤትና ከቤት ሆነው የቤተ መጻሕፍታቸውን ድረ ገጽና በዚያ የተዘረዘሩ የመረጃ ምንጮችን በማየት እንዲጠቀሙበት ይበረታታሉ።

**<u>የአንደኛ ደረጃ የሞንቴሶሪ ፕሮግራም (ቅድመ አፀደ ሕጻናት እና አፀደ ሕጻናት) 703-228-8632</u>**

በማሪያ ሞንቴሶሪ ስራ ላይ የተመሰረተው የሞንቴሶሪ ትምህርት ከአንድ በላይ እውቀትን የሚሸፍንና ለተለያየ ዕድሜ የሚሆን የመማር አቀራረብ ነው። ተማሪዎች በራሳቸው ፍጥነት እንዲሰሩ በሚፈቅድላቸው በተዘጋጀ አካባቢ ውስጥ በተናጠል እና በትብብር ይሰራሉ። የሞንቴሶሪ የማስተማሪያ ማቴሪያሎች የሚዘጋጁት ትኩረት የማድረግ፣ የተነሳሽነት፣ የፅናትና አዲስ ነገር የማፍለቅ ልማዶችን ለማሳደግ ሲሆን፣ የሞንቴሶሪ ፍልስፍና እና ማሕበረሰብ አጽንኦት የሚሰጠው ደግሞ ሌሎችን፣ ሰላም እና ፈጣሪነትን ለማክበር ነው።

ለሶስት፣ አራት እና አምስት ዓመት ልጆች የሞንቴሶሪ ፕሮግራሞች የሚሰጡት በአርሊንግተን የሞንቴሶሪ የሕዝብ ት/ቤት እና በ Barrett, Carlin Springs, Discovery, Fleet, Oakridge እና Jamestown አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ውስጥ ነው። የአርሊንግተን ነዋሪዎች የቅበላ ዓመቱ ሴፕቴምበር 30 ድረስ ሶስት ዓመት እስከሞላቸው ድረስ ለቅበላ ብቁ ናቸው። ዕድሜያቸው ለቅድመ አፀደ ሕጻናት የደረሱ ለጆች የትምህርት ክፍያ የሚታሰበው በገቢ መሰረት ይሆናል። ክፍት የስራ ቦታዎች ውስጥ ሁለት ሶስተኛው የሚያዝላቸው ቤተሰቦቻቸው የገቢ ብቁነት መመሪያዎችን ለሚያሟሉ ልጆች ነው።

በማመልከቻው ወቅት ማመልከቻዎችን በቀጣዩ ድረገጽ በኩል ማቅረብ ይቻላል፦ [https://apsva.schoolmint.net/sign in](https://apsva.schoolmint.net/sign in) የቀረቡት ማመልከቻዎች ቁጥር ካሉን ክፍት ቦታዎች ከበለጠ፣ በእጣ የምንለይ ይሆናል።

# ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች

ስለ ፕሮግራሙ ወይም የማመልከቻ ሒደት ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የAPS ድረ ገጽን http://www.apsva.us/earlychildhood ወይም https://www.apsva.us/school-options/elementary-school-choices ይጎብኙ ወይም ለቅድመ ልጅነት ቢሮ በስልክ ቁጥር 703-228-8632 ይደውሉ።

## <u>የባለ ተሰጥኦ ተማሪዎች አገልግሎቶች 703-228-6160</u>

እያንዳንዱ ት/ቤት ተሰጥኦ እንዳላቸው ለተለዩ ተማሪዎች የተለየ ትምህርት ያቀርባል። ት/ቤት ተኮር አገልግሎቶች የሚሰጡት በመደበኛው የመማሪያ ክፍል አቀማመጥ ሆኖ፣ የተለዩ ተማሪዎችም ባላቸው ጥንካሬ መሰረት ለአንድ የተወሰነ ትምህርት በቡድን እንዲደራጁ ይደረጋል (በአንድ ክላስተር ውስጥ ቢያንስ 10 ተማሪዎች ይመደባሉ)። የክላስተር መምህራን የባለተሰጥኦ ተማሪዎችን መገለጫ ባህሪያት በተመለከተና ባለተሰጥኦ ተማሪዎች ያላቸውን የተለያዩ ፍላጎቶች ለማሟላት ስለሚያስችሉ ምርጥ ተሞክሮዎች ስልጠና ይሰጣቸዋል። የክላስተር መምህራን ለባለተሰጥኦ ተማሪዎች የተጻፈ ስርዓተ ትምህርት እና አጋዥ ግብዓቶችን በተመለከተም ስልጠና የሚሰጣቸው ሲሆን፣ ጥልቅ እና/ወይም ፈጠራዊ አስተሳሰብ፣ ችግር አፈታት፣ የመመርመርና ጥናት የማድረግ ክህሎቶችን በመጠቀም አጠቃላይ የትምህርት ስርዓተ ትምህርቱን የሚሸፍንና የሚያበለጽግ የላቀ ይዘትና ፅንሰ ሃሳቦች ላይም ያተኩራል። አግባብነት ሲኖረው፣ ተጨማሪ የማፋጠን ዕድሎችም ሊፈተሹ ይችላሉ።

ለባለተሰጥኦ ተማሪዎች የሚመደቡ ባለ ልዩ ችሎታ መምህራን የእያንዳነዱ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ሰራተኞች የማይነጣጠሉ አካላት ናቸው። ትብብር ላይ የተመሰረተ የእቅድ ዝግጅት እና/ወይም በትብብር የማስተማር ሞዴልን በመጠቀም፣ የክፍል ሃላፊና የባለተሰጥኦ ተማሪዎች መምህሩ አብረው በመስራት የላቀ ብቃት ላላቸው ተማሪዎች የተጻፈ ስርዓተ ትመህርትን በዕለታዊ ተማሪዎችን የመለያ ትምህርት ውስጥ ያካትታሉ። የባለተሰጥኦ ተማሪዎች መምህራን ለሁሉም መምህራን የተዘጋጁ ፈጠራዊ የአስተሳሰብ ስትራቴጂዎችና ትምህርቶችን በመጠቀም እነዚህ ስትራቴጂዎች በትምህርት ዘመኑ ውስጥ ወደነዚህ ስትራቴጂዎች እንዲካተቱ የመደገፍ ግብን ያሳካሉ።

በእያንዳንዱ የትምህርት ዘመን ተማሪዎች ወደ ባለተሰጥኦ አገልግሎቶች የሚመደቡት በእንግሊዝኛ፣ ሒሳብ፣ ማሕበራዊ ጥናቶች እና ሳይንስ የአካዳሚክ ዘርፎች ለ K-12 እና ለስነ ጥበብ እና/ወይም ሙዚቃ ደግሞ ለ3ኛ-12ኛ ክፍሎች ነው። ብቁ ለመሆንና አገልግሎት ለማግኘት የተቀመጡ የተለያዩ መስፈርቶችን የተመለከተ ተጨማሪ መረጃ የባለተሰጥኦ አገልግሎቶች ድረ ገጽ ላይ ይገኛል፡- http://www.apsva.us/giftedservices ወይም ልጅዎ የሚማርበት ት/ቤት ውስጥ የሚገኝ የባለተሰጥኦ ተማሪዎች መምህርን በማነጋገር መረጃ ማግኘት ይቻላል።

## <u>የበጋ ትምህርት (አንደኛ ደረጃ) 703-228-7645</u>

የአንደኛ ደረጃ የበጋ ትምህርት የሚሰጣቸው የተለዩ ተማሪዎች ከቅድመ አፀደ ሕጻናት ጀምሮ እስከ 5ኛ ክፍል ድረስ ላሉት ሲሆን፣ ዓላማውም የአካዳሚክ ብቃታቸውን ማሻሻል የሚያስፈልጋቸውን ተማሪዎች ለማገዝ ነው።

የበጋ ት/ቤትን አድራሻና የትምህርት ጊዜ ጨምሮ ትምህርትን የሚመለከት መረጃ በየዓመቱ የካቲት ወር ላይ በ APS ድረ ገጽ ላይ የሚለጠፍ ሲሆን፣ በሁሉም የ APS ት/ቤቶች ውስጥም ይገኛል። ልጀዎ የበጋ ትምህርት ለመከታተል ብቁ ከሆነ፣ ልጅዎ ለፕሮግራሙ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ በሚማርበት ት/ቤት መመዝገብ አለበት።

የበጋ ት/ቤት ፕሮግራም የጊዜ ገደብ በየዓመቱ የሚቀያየር ሲሆን ቀነ ገደቡም በጥብቅ ተፈጻሚ ይደረጋል። ከተመደቡበት የበጋ ት/ቤት ከአንድ ማይል ርቀት በላይ ለሚኖሩ የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች የትራንስፖርት አገልግሎት ይቀርባል። ተማሪዎች ለትራንስፖርት አገልግሎት በቁ ለመሆን በካውንቲ አቀፍ ፕሮግራም ላይ መሳተፍ ወይም በት/ቤታቸው ውስጥ መመዝገብ አለባቸው። ለአንደኛ ደረጃ የበጋ ት/ቤት ፕሮግራም ከትምህርት በፊትና በኋላ የተራዘመ የሕጻናት እንክብካቤ አገልግሎት ይቀርባል።

## የፌዴራል እና የስቴት ፕሮግራሞች

**ርዕስ I 703-228-6161**

በ2015 በወጣው የፌዴራል *Every Student Succeeds ሕዋጅ (ESSA)* ርዕስ I ፕሮግራም አማካይነት፣ ቢያንስ 45% የሚሆኑት ተማሪዎቻቸው በኢኮኖሚ የተጎዱ የሆኑባቸው የአርሊንግተን አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች የፕሮግራሙን ግቦች ለማሳካት የሚያስችል ተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ብቁ ይሆናሉ። በአሁኑ ጊዜ ስምንት ት/ቤቶች በርዕስ I ፕሮግራም ውስጥ ይሳተፋሉ።

የርዕስ I ፕሮግራም ተቀዳሚ ግብ በት/ቤት ውስጥ ያሉ ሁሉንም ተማሪዎች አካዳሚክ ስኬት መደገፍ ሲሆን፣ በክፍል ደረጃ ማንበብና መጻፍ እንደዚሁም ቀላል የሒሳብ ስሌቶችን ለማሳካት ጉዳይ የተለየ ትኩረት ይሰጠዋል። በተጨማሪም፣ ርዕስ I የተማሪዎችን ትምህርት የማፋጠን፣ ስኬትን የማሳደግ፣ የተማሪ ደህንነትን የመደገፍና የእድሎችና የስኬት ክፍተቶችን የማስቀረትን የAPS አቀፍ ጥረቶች ለመደገፍ ቁርጠኛ ነው። እነዚህን ግቦች ለማሳካት የሚያግዘው የባለብዙ ዘርፍ ርዕስ I ፕሮግራም ዋና ዋና ክፍሎች የሚከተሉት ናቸው:-

- ለሁሉም ተማሪዎች ከፍተኛ የአካዳሚክ መለኪያዎች አሉት፤
- ለሁሉም ተማሪዎች ስሜታዊ የትምህርት ድጋፎች መስጠት፤
- የማስተማር ዕቅድ ዝግጅትን ለማሳወቅ የተማሪ ግንዛቤ ላይ ቀጣይነት ያለው ምዘና እና ትንታኔ ማካሄድ፤
- ከፍተኛ ስልጠና ያላቸው ሰራተኞች የሚሰጡት ሁሉን አቀፍ የማንበብና መጻፍ እና የሒሳብ ትምህርት ድጋፍ፤
- በማስጠናትና በበጋ ፕሮግራም ዝግጅት አማካይነት ለተራዘመ ትምህርት የሚሰጥ ድጋፍ፤
- ዘላቂና ስራ ላይ ያተኮረ ሙያዊ ትምህርት፤
- በቤት እና ት/ቤት መካከል ስኬታማ አጋርነትን ለመደገፍ ከቤተሰቦች ጋር የሚኖር ተሳትፎ፤ እና
- ት/ቤቶች እነዚህን ግቦች እንዲያሳኩ ማገዝ የሚችሉ ድርጅቶች ጋር የሚፈጠሩ የማሕበረሰብ አጋርነቶች።

ስለ ርዕስ I ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ ቀጣዩን ድረ ገጻችንን ይጎብኙ:- www.apsva.us/titleI።

**ቨርጂኒያ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ኢኒሼቲቭ (VPI) ቅድመ-አፀደ ሕጻናት**

አርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች ከቨርጂኒያ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ኢኒሼቲቭ (VPI) ጋር በመተባበር እስከ ሴፕቴምበር 30 ድረስ አራት ዓመት ለሞላቸውና ዝቅተኛ ገቢ ካላቸው ቤተሰቦች ለተገኙ ልጆች የቅድመ አፀደ ሕጻናት ትምህርት ያቀርባል። የቅድመ አፀደ ሕጻናት ስርዓተ ትምህርት በጥናት ላይ የተመሰረተ፣ የማንበብና መጻፍና የሒሳብ ክህሎት እድገትን የሚያጎለብትና ለዕድሜ ልክ ትምህርት ማሕበረ-ስሜታዊ መሰረቶችን የሚጥል ነው።

ትምህርቶቹ የሚሰጡት በአስራ አምስት የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ውስጥ ሲሆን ከሰኞ እስከ አርብ ያለውን የት/ቤት መርሃ ግብር ይከተላሉ። እያንዳንዱ ክፍል 18 ልጆችን የሚይዝ ሲሆን፣ የብቃት ማረጋገጫ ያለው መምህርና የሙሉ ጊዜ የመምህር ረዳትም አብረው ይኖራሉ። የትራንስፖርት አገልግሎት የሚቀርብላቸው ተማሪዎች በአቴንዳንስ ቀጠና የሚኖሩ ወይም የካውንቲ አቀፍ ሳይት ውስጥ የሚኖሩ ናቸው። በሁሉም ት/ቤቶች ውስጥ አራት ዓመት ለሆናቸው ልጆች ከመደበኛው ሰዓት ያለፈ እገዛ ይቀርብላቸዋል።

ማመልከቻ ለማስገባት፣ ከየካቲት 1 እስከ ኤፕሪል ባለው የማመልከቻ ጊዜ ውስጥ በቀጣዩ ድረ ገጽ የኦንላይነ ማመልከቻ ያስገቡ:- https://apsva.schoolmint.net 15. የቀረቡት ማመልከቻዎች ካሉን ቦታዎች ቁጥር ከበለጡ፣ በእጣ የመለየት ሒደት እንከተላለን። ከኤፕሪል 15ኛ በኋላ፣ ማመልከቻዎችን የምንቀበለው ባሉን ቦታዎች ላይ ተመስርተን ነው። የፕሮግራም ወይም የማመልከቻ ሒደትን በተመለከተ ለተጨማሪ መረጃ፣ እባክዎ ቀጣዩን የAPS ድረ ገጽ ይጎብኙ:- www.apsva.us/earlychildhood ወይም ለቅድመ ልጅነት ቢሮ በስልክ ቁጥር 703-228-8632 ይደውሉ።

# ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች

**<u>የተራዘመ ቀን 703-228-6069</u>**

የአርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች የተራዘመ ቀን ፕሮግራም ወላጆቻቸው ተቀጣሪ ለሆኑ፣ ትምህርት ላይ ላሉ ወይም አቅም ለሌላቸው የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች በክትትል ስር ከትምህርት ሰዓት ውጭ ፕሮግራም ያመቻቻል። በAPS የቅድመ አፀደ ሕጻናት ፕሮግራሞች ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች የተራዘመ ቀን አገልግሎት ለማግኘት እስከ ሴፕቴምበር 30 ድረስ ዕድሜያቸው አራት ዓመት መሙላት አለበት። ፕሮግራሙን የሚመሩት የአርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች ሰራተኞች ሲሆኑ፣ የእያንዳንዱን ተማሪ ፍላጎት ለማሟላት ተብለው የተቀረጹ ዕለታዊ የመዝናኛና አበልጻጊ የሐብት ግንባታ ተግባራትን ያቀፈ ነው። ይህ የአገልግሎት ክፍያ የሚከፈልበት ፕሮግራም ነው።

የተራዘመ ቀን በእያንዳንዱ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ ከት/ቤት ፕሮግራም በፊትና በኋላ መደበኛ ፕሮግራም በተያዘላቸው የትምህርት ቀናት ይሰጣል። ከት/ቤት ፕሮግራም በፊት ያለው ትምህርት 7 am ላይ ጀምሮ የትምህርት ቀን እስከሚጀምር ድረስ ይቆያል። ድሕረ ት/ቤት ፕሮግራሞች ተማሪዎች ትምህርት ጨርሰው ሲወጡ ይጀምርና እስከ 6 pm ድረስ ይቆያል። በበጋ ወቅት፣ የተራዘመ ቀን በእያንዳንዱ የአንደኛ ደረጃ የበጋ ት/ቤት ቦታ ላይ ከት/ቤት ፕሮግራሞች በፊትና በኋላ ይካሄዳል።

የአርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች ዝግ ሲሆኑ፣ ሁሉም የተራዘመ ቀን ፕሮግራሞቸ ይዘጋሉ። የአርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች የትምህርት መጀመሪያ ጊዜ እንደሚዘገይ ካሳወቁ፣ ከትምህርት ክፍለ ጊዜ በፊት ያለው የተራዘመ ቀን በተመሳሳይ የሰዓት መጠን ይዘገያል። የአርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች ከመደበኛው የጊዜ ሰሌዳ አስቀድመው ከዘጉ፣ የተራዘመው ቀን ፕሮግራሞች የሚዘጉት 4 pm ነው።

ቤተሰቦች በተራዘመ ቀን ፕሮግራም ውስጥ ለመሳተፍ በፀደይ ወቅት የማመልከቻ መስኮት መካከል ባለው በየትኛውም ጊዜ የምዝገባ መረጃ ማስገባት ይችላሉ። በማመልከቻው ወቅት የደረሱ ምዝገባዎች በሙሉ በእኩልነት ይስተናገዳሉ። ለቀረቡ የምዝገባ ጥያቄዎች በቂ ቦታ ባላቸው ት/ቤቶች፣ የማመልከቻ ቀነ ገደቡ ውስጥ ያመለከቱ ሁሉም ልጆች ይመዘገባሉ። ካላቸው ክፍት ቦታ በላይ የምዝገባ ጥያቄ ለሚቀርብላቸው ት/ቤቶች፣ የማመልከቻ ቀነ ገደቡ ውስጥ ያመለከቱ ሁሉም ልጆች በነሲባዊ የእጣ ማውጣት ሒደት ይለያሉ። የምዝገባ ማመልከቻ በኦንላይን ማቅረብ ይቻላል፡- http://www.apsva.us/extended-day/

ለተጨማሪ መረጃ፣ ቀጣዩን የተራዘመ ቀን ፕሮግራም ድረ ገጽ ይጎብኙ http://www.apsva.us/extended-day/ ወይም በስልክ ቁጥር 703-228-6069 ይደውሉ።

**<u>የልዩ ፍላጎት ትምህርት 703- 228-6040</u>**

የአርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች ዕድሜያቸው ከሁለት እስከ ሃያ አንድ ዓመት ለሆናቸው፣ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ለሚያስፈልጋቸውና በካውንቲው ውስጥ ለሚኖሩ ሁሉም አካል ጉዳተኞች ከክፍያ ነጻና አግባብነት ያለው ትምህርት ለመስጠት ቁርጠኛ ነው። (ዕድሜው ከ2 እስከ 21 ዓመት የሆነ ልጅ ማለት የሁለተኛ ዓመት የልደት በዓሉ ሴፕቴምበር 30 ላይ ወይም ከዚያ በፊት የተከበረ ልጅ ማለት ነው። አካል ጉዳት ያለበት/ያለባት ልጅዎ ከሴፕቴምበር 30 በኋላ እድሜው/እድሜዋ 22 ዓመት ከሞላ፣ ለዚያ የትምህርት ዘመን አገልግሎት ለማግኘት ብቁ ይሆናል ወይም ትሆናለች።) በተጨማሪም፣ በአርሊንግተን ካውንቲ ወሰን ውስጥ በሚገኙ የግል ት/ቤቶች ውስጥ በወላጆቻቸው የተመዘገቡ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች በ APS በሚዘጋጅ የግለሰባዊ አገልግሎቶች እቅድ አማካይነት የልዩ ፍላጎት ትምህርት ይቀርብላቸዋል። የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን የተለዩ ትምህርታዊ ፍላጎቶች በሚገባ ለማሟላት፣ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች ሙሉ ጥቅል ይቀርባል። አግባብነት ባለው መጠን ድረስ፣ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች በአጠቃላይ የትምህርት ከባቢ ውስጥ የሚስተናገዱ ሲሆን፣ ጉዳት አልባ ከሆኑ አቻዎቻቸው ጋር አብረው ይማራሉ።

የተማሪ ድጋፍ ሰጪ ቡድኖች (SST) በሁሉም ት/ቤቶች ውስጥ የሚመሰረቱ ሲሆን አስቸጋሪ ሁኔታ የሚያጋጥማቸውን ተማሪዎች ሪፈራል ተቀብለው እርምጃ ይወስዳሉ። እነዚህ ኮሚቴዎች አካል ጉዳተኝነት እንዳለባቸው የሚጠረጠሩ ተማሪዎችን ወደ ት/ቤት ተኮር የልዩ ፍላጎት ትምህርት ብቁነት ኮሚቴ ሊያስተላልፉ ይችላሉ። እንደዚህ ዓይነት ሪፈራል በተማሪው ላይ የሚደረጉ የጤና፣ ማሕበረ ባሕላዊ፣ ስነልቡናዊ እና ትምህርታዊ ግምገማዎችን የሚያካትት መደበኛ ምዘና ከመካሄዱ በፊት የወላጅ ፈቃድን ይጠይቃል። ብቁነትን የሚወስነው ኮሚቴ ተማሪው የልዩ ፍላጎት ትምህርት እና/ወይም ተዛማጅ አገልግሎቶች የሚያስፈልገው ትምህርታዊ አካል ጉዳት ያለበት መሆኑን ለመወሰን እንዲችል አስፈላጊ የምዘና መረጃዎችን ይዳስሳል። ለመጀመሪያ ጊዜ ብቁ ለመሆን የወላጅ ፈቃድ ያስፈልጋል።

## ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች

አንድ ተማሪ የልዩ ፍላጎት ትምህርት የሚያስፈልገው ትምህርታዊ አካል ጉዳት እንዳለበት ከተለየ፣ ግለሰባዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ይዘጋጃል። IEP የሚዘጋጀው በ IEP ቡድን ሲሆን ወላጆችም የቡድኑ አባላት ናቸው። በጽሑፍ የሚዘጋጀው ሰነድ ተቀዳሚ ዓላማ የተለየውን ተማሪ ፍላጎቶች መግለጽና እነዚህን ፍላጎቶች የሚያሟሉትን የተወሰኑ የልዩ ፍላጎቶ ትምህርቶች እና መስተንግዶዎች ማስረዳት ነው። የ IEP ትግበራ የወላጆችን ፈቃድ ይጠይቃል። የ IEP ቡድን እንዳግባብነቱ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ በ IEP ላይ ዳሰሳና ክለሳ ያካሂዳል።

IEP ያላቸው አብዛኞቹ ተማሪዎች የሚስተናገዱት በአጠቃላይ ትምህርት ማዕቀፍ ነው። ይሁን እንጂ፣ የተማሪው ፍላጎቶች አስፈላጊ ካደረጉት በልዩ ትምህርት ማዕቀፍ ውስጥ አገልግሎቶች ሊሰጡ ይችላሉ። ስለዚህ፣ ት/ቤቶች በአጠቃላይ ትምህርት እና በልዩ ትምህርት ማዐቀፍ ውስጥ ተከታታይ አገልግሎቶችን ያቀርባሉ። በተጨማሪም፣ ተማሪዎች በIEP ቡድናቸው የተቀመጡላቸውን ግቦች ለማሳካት የልዩ ፍላጎት ወይም ጥልቀት ያለው የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች ሊያገኙ ይችላሉ። ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች ፍላጎቶች ይበልጥ ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማሟላት፣ APS የተለያዩ ፕሮግራሞችን አስቀምጧል። እነዚህ ፕሮግራሞች ተማሪዎች ከግለሰባዊ ፍላጎቶቻቸው ጋር የሚጣጣሙ ወጥ እና ውጤታማ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ያስችሏቸዋል። እያንዳንዱ ፕሮግራም የተወሰኑ የተማሪውን ፍላጎቶች የሚያስተናግድ በልዩ ሁኔታ የተዘጋጀ ትምህርት ይቀርባል፣ የማስተማር መለኪያዎች ወይም የተጣጣመ የትምህርት መለኪያዎች ስርዓተ ትምህርትን ይከተላል። አንድ ተማሪ ወደ ፕሮግራሙ የሚመደበው በ IEP ቡድን በሚሰጥ ጥንቃቄ የተሞላበት ውሳኔ ነው፤ ምክንያቱም እንደዚህ ዓይነት ፕሮግራሞች ይበልጥ ገዳቢ የሆነ ምደባን ይወክላሉ።

አሁን ያሉ ፕሮግራሞች አጭር መግለጫዎች ከዚህ በታች ቀርበዋል። የፕሮግራም መማሪያ ክፍሎች ራሳቸውን የቻሉ ማዕቀፎች ተደርገው ይቆጠራሉ፤ የማካተቻ እድሎች ግን እንዳግባብነቱ ለእያንዳንዱ ተማሪ ይፈለጋሉ። ሁሉም የፕሮግራም መማሪያ ክፍሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ክፍሎቹ የሚገኙበት ሕንጻ ርዕሰ መምህር ሲሆን ከልዩ ፍላጎት ትምህርት ጽ/ቤት ድጋፍ ይደረግለታል። እያንዳንዱ የፕሮግራም መማሪያ ክፍል አንድ መምህር እና አንድ ወይም ሁለት የመማሪያ ክፍል ረዳቶች ይኖሩታል። እያንዳንዱ ፕሮግራም ከልዩ ፍላጎት ትምህርት ጽ/ቤት በሚመጡ ተጨማሪ ሰራተኞች የሚደገፍ ሲሆን፣ የተዛማጅ አገልግሎት አቅራቢዎች፣ የአካል ጉዳትና የባህርይ ስፔሻሊስቶችና የልዩ ፍላጎት ትምህርት እድሎችን ይጨምራል።

ከካውንቲ አቀፍ ፕሮግራሞች በተጨማሪ፣ APS አካል ጉዳት ላይ ብቻ ያተኮሩ አገልግሎቶችን ሞዴል የቀረጸ ሲሆን ይህም የማየት ወይም የመስማት ውስንነት ላለባቸውና አጠቃላይ የትምህርት ማዕቀፉን ለመድረስ መስተንግዶና አገልግሎቶች ለሚያስፈልጋቸው የልዩ ፍላጎት ትምህርት ተማሪዎች ድጋፍ የሚሰጥ ነው። ይህ የተከማቸ አገልግሎቶች ሞዴል አገልግሎቶችን (የብሬል ጽሁፍ መገልበጥ ወይም የምልክት ቋንቋ ማስተርጎም) እንደዚሁም አካባቢያዊ መስተንግዶዎችን (ብርሃን ወይም የሚረብሽ ድምፅን የመላመድ ችሎታ) በመስጠት ምሪትን የሚደግፍና ወደ ሕንጻው አስተማማኝ ተደራሽነትን የሚያረጋግጥ ነው። ይህ ሞዴል ለተማሪዎች ቀጥተኛ አገልግሎቶችን ከመስጠቱ በተጨማሪ፣ ሙያዊ ማጎልበቻ በአጠቃላይ እና ልዩ ትምህርት መምህራንና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ላይ የሚኖረውን ተጽእኖ ያሳድጋል። እባክዎ ያስታውሱ፡- አድራሻዎች እዚህ ላይ ያልተጠቀሱት ሊለወጡ ስለሚችሉ ነው።

*በአርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች ውስጥ ስለሚሰጥ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ተጨማሪ መረጃ* በ APS ድረ ገጽ [www.apsva.us](www.apsva.us) ላይ በልዩ ፍላጎት ትምህርት ጽ/ቤት ስር ይገኛል ወይም በስልክ ቁጥር 703-228-6040 በመደወል ወይም ለ APS የልዩ ፍላጎት ትምህርት የወላጆች መረጃ ማዕከል በስልክ ቁጥር 703-228-7239 በመደወል ማግኘት ይቻላል።

### <u>የልዩ ፍላጎት ትምህርት፡- ቅድመ - አፀደ ሕጻናት</u>

የ APS የቅድመ አፀደ ሕጻናት የልዩ ፍላጎት ትምህርት ፕሮግራም ቁጥጥር የሚደረግበት ከልዩ ፍላጎት ትምህርት ጽ/ቤት ነው። ፕሮግራሙ ዕድሜያቸው ከሁለት እስከ አራት ዓመት ለሆናቸው አካል ጉዳተኛ ልጆች አገልግሎት ይሰጣል። በተማሪው ፍላጎቶች እና በግለሰባዊ የትምህርት ዕቅዶች (IEPs) ላይ በመመስረት የተለያዩ የፕሮግራም አማራጮች አሉ። ካሉት አማራጮች መካከል በአርሊንገተን ውስጥ በሚገኝ የልጁ የግል የሕጻናት እንክብካቤ መስጫ ቦታ ወይም በቅድመ አፀደ ሕጻናት ፕሮግራም፣ የጨቅላ ሕጻናት ፕሮግራሞች፣ ኦቲዝም ላለባቸው ልጆች የሚቀርቡ ከአንድ በላይ እርምጃ የሚወሰድባቸው ፕሮግራሞች፣ ጥልቀት ያላቸውና ራሳቸውን የቻሉ ፕሮግራሞችና የማህበረሰብ አቻ ፕሮግራሞች ውስጥ ዕድሜያቸው ከሶስት እስከ አራት ዓመት ለሆኑ ልጆች የሚቀርቡ ማህበረሰብ ተኮር የመረጃ አገልግሎቶችን ይጨምራል። ዕድሜያቸው ከሶስት እስከ አራት ዓመት ለሆናቸው ልጆች የሚዘጋጁ ፕሮግራሞች ከ VPI ስርዓተ ትምህርት ጋር የተጣጣሙ ናቸው። የቅድመ አፀደ ሕጻናት የልዩ ፍላጎት ትምህርት ፕሮግራም ግቡ ተማሪዎች በተለዩ የዕድገት መዘግየት ያለባቸው መስኮች ውስጥ የተቀመጡላቸውን የተናጠል የ IEP ግቦች እንዲያሳኩ ለማገዝ ነው።

### <u>የልዩ ፍላጎት ትምህርት፡- የቅድመ መደበኛ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ፕሮግራም፡- ሚኒ MIP-A (Pre-K)</u>

የኦቲዝም ስፔክትረም ዲስኦርደር (Mini MIP-A) ላለባቸው ተማሪዎች የተዘጋጀው አነስተኛ ባለብዙ ጣልቃ ገብነት ፕሮግራም የኦቲዝም ስፔክትረም ዲስኦርደር ያለባቸውን የተወሰኑ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተማሪዎች ፍላጎት ለማሟላት የተቀረጹ ናቸው። የፕሮግራሙ ግቦች ውስጥ ከሚካተቱት መካከል በተግባቦት፣ ተላማጅ ባህርይ፣ ራስን ችሎ እና ከሌሎች ልጆች ጋር የመጫወት ችሎታ ላይ ማተኮር ይገኙበታል። የ Mini MIP-A የመማሪያ ክፍሎች ተማሪዎችን አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ለማዘጋጀት እጅግ መዋቅሩን በጠበቀ ማዕቀፍ ስር የተለያዩ ማስረጃ ተኮር ስትራቴጂዎችን ይጠቀማሉ። በፕሮግራሙ ውስጥ ያሉትን እያንዳንዱን ተማሪ ፍላጎቶች ለማሟላት ሲባል ስትራቴጂዎች ተመርጠው ግለሰባዊ ይደረጋሉ። ከእነዚህ ስትራቴጂዎች ምሳሌዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡- አፕላይድ የባህርይ ትንተና (ABA)፣ የምስል ልውውጥ የተግባቦት ስርዓት (PECS) እና ምስላዊ ድጋፎች።
የእነዚህንና ሌሎች ጥቅም ላይ ሊሉ የሚችሉ እርምጃዎችን ዝርዝር ማብራሪያ ለማግኘት፣ እባክዎ ይህን ማስፈንጠሪያ ይከተሉ፡-
[http://autismpdc.fpg.unc.edu/evidence-based-practices.](http://autismpdc.fpg.unc.edu/evidence-based-practices.)

# ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች

**<u>የልዩ ፍላጎት ትምህርት፦ መስማት የተሳናቸው እና ከባድ የመስማት ችግር ያለባቸው</u>**

መስማት የተሳናቸው እና ከባድ የመስማት ችግር ያለባቸው ፕሮግራም የተቀረጸው መስማት ለተሳናቸው ወይም ከባድ የመስማት ችግር ላለባቸውና ልዩ በቋንቋ የበለጸገ ፕሮግራም ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ነው። መስማት የተሳናቸው እና ከባድ የመስማት ችግር ያለባቸው (TDHH) መምህር የሚደገፍ ሆኖ ከንግግር-ቋንቋ ፓቶሎጂስት እና ኦዲዮሎጂስት ጋር በመተባበር የሚሰጥ ነው። የፕሮግራሙ ግብ የተማሪዎችን የቋንቋና የተግባቦት ክህሎቶች ማሻሻልና ለአጠቃላይ ትምህርት ስርዓተ ትምህርት ሙሉ ተደራሽነትን መፍጠር ነው። የምልክት ቋንቋ፣ የከንፈር ንቅናቄና የእጅ እንቅስቃሴን ያጣመረ ንግግር (cued speech)፣ የእንግሊዝኛ ንግግር፣ እና/ወይም የእይታ ኢጋዥ መሳሪያዎች ተማሪዎች ለስርዓተ ትምህርት ያላቸውን ተደራሽነት ለመደገፍ ይውላሉ።

**<u>የልዩ ፍላጎት ትምህርት፦ ተግባራዊ የሕይወት ክህሎቶች ፕሮግራም</u>**

በአንደኛ ደረጃ የ FLS ፕሮግራም ትኩረት መሰረታዊ የአካዳሚክ ክህሎቶችን መሰረት መጣል፣ ዕለታዊ የኑሮ ክህሎቶችን፣ ተግባቦት፣ የጡንቻ/የእንቅስቃሴ ክህሎቶችን እና የስሜት ሕዋሳትን ዕድገት መጨመር ነው። በአስተውሎት ወይም በአእምሯዊ አካል ጉዳት፣ የስሜት ሕዋሳት ውስንነት፣ የአጥንት ጤና ውስንነት ወይም በሌሎች የጤና እክሎች ምክንያት የልዩ ፍላጎት ትምህርት ድጋፍ የሚያገኙ ተማሪዎች ለተግባራዊ የሕየወት ክህሎቶች ፕሮግራም ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ፕሮግራሙ ሲበዛ ግለሰባዊ የሆነ የትምህርት ፕሮግራምን ጥልቅ ከሆኑ ተዛማጅ አገልግሎቶች ጋር ያቀርባል። በአንደኛ ደረጃ የሚሰጥ FLS የተለያዩ በጥናት የሚደገፉ ስርዓተ ትምህርቶችና አሰራሮችን ይጠቀማል፤ ለምሳሌ ለአካዳሚክ እና ለቅድመ ሞያ ክህሎቶች የሚሆን ልዩ የመማሪያ ስርዓተ ትምህርት። አንዱ የትምህርት አሰጣጥ ክፍል በመሆኑ፣ ልዩ ትምህርት ወሳኝ በሆኑት የማንበብ፣ መጻፍ፣ ሒሳብ፣ ሳይንስ እና ማሕበራዊ ጥናቶች ውስጥ ግለሰባዊ ምዘና፣ ክትትል እና ትምህርቶችን ያቀርባል። ቡድን ተኮር የሆነው አቀራረብ የተማሪዎችን ፍላጎቶች ለማሟላት የሚያስችሉ የትምህርት እቅዶችን ለማዘጋጀት የተለያዩ ስትራቴጂዎችና የጣልቃ ገብ እርምጃዎች ላይ የተመሰረተ ነው።

**<u>የልዩ ፍላጎት ትምህርት፦ የእረፍት ሰዓት ፕሮግራም</u>**

የእረፍት ሰዓት ፕሮግራም ትኩረቱ በስነልቡናዊ ወይም ባህሪያዊ የጤና መዛባቶች ምክንያት ከፍተኛ የሆነ ጣልቃ ገብ ባህሪያት ባለባቸው ተማሪዎች ውስጥ ማሕበራዊና ስሜታዊ ትግበራን ማሻሻል ነው። በስሜታዊ አካል ጉዳት ወይም ከፍተኛ በሆነ ባህሪያዊ ችግር ምክንያት የልዩ ፍላጎት ትምህርት ድጋፍ የሚያገኙ፣ ነገር ግን የአካዳሚክ ክህሎታቸው የክፍል ደረጃቸው ጋር የሚመጥን ወይም የሚቀራረብ ተማሪዎች ለእረፈት ሰዓት ፕሮግራም ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ፕሮግራሙ ተማሪዎች ግለ ጽንሰ ሃሳብን እንዲያሻሽሉ፣ አዎንታዊ ግንኙነቶችን እንዲያዳብሩና አካዳሚያዊ ስኬት እንዲያስመዘግቡ የሚያግዝ የማገገሚያ ከባቢ ይፈጥራል። ቡድን ተኮር የሆነው አቀራረብ በአካዳሚክ፣ ክሊኒካዊ፣ ኢንተራኤጀንሲ እና የቤተሰብ ኢጋዥ ግብዓቶች ላይ ተመስርቶ የተማሪዎችን ፍላጎቶች የሚያስተናግድ ትምህርታዊ ፕሮግራም ያዘጋጃል።

**<u>የልዩ ፍላጎት ትምህርት፦ ኦቲዝም ላለባቸው ተማሪዎች የሚዘጋጅ ባለብዙ እርምጃ ፕሮግራም (MIPA)</u>**

የ MIPA ፕሮግራም ዋና ትኩረት ተማሪዎች የተግባቦት ክህሎት፣ ራስን የመቻል የሕይወት ክህሎቶች፣ ማሕበራዊ ክህሎቶች እና አካዳሚያዊ ብቃትን የሚያሳድጉበት እድልና አካባቢ መፍጠር ነው። በትምህርታዊ የኦቲዝም መለያ ምክንያት የልዩ ትምህርት ድጋፍ የሚያገኙ ተማሪዎች ለ MIPA ፕሮግራም እጩ ሊሆኑ ይችላሉ። ፕሮግራሙ በከፍተኛ ደረጃ የተዋቀረ አካባቢን የሚፈጥር ሲሆን፣ የኦቲዝም ስፔክትረም ዲስኦርደር ላለባቸው ተማሪዎች የተለያዩ ማስረጃ ተኮር አካዳሚክና ባህሪያዊ ጣልቃ ገብነቶችን ይጠቀማሉ። በፕሮግራሙ ውስጥ ያሉትን እያንዳንዱን ተማሪ ፍላጎቶች ለማሟላት ሲባል ስትራቴጂዎች ተመርጠው ግለሰባዊ ይደረጋሉ። ከእነዚህ ስትራቴጂዎች ምሳሌዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፦ አፕላይድ የባህርይ ትንተና (ABA)፣ የምስል ልውውጥ የተግባቦት ስርዓት (PECS) እና ምስላዊ ድጋፎች። እነዚህንና ሌሎች ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ጣልቃ ገብ እርምጃዎችን በተመለከተ ዝርዝር ማበራሪያ ለማግኘት፣ እባክዎ ይህን ማስፈንጠሪያ ይከተሉ፦ [http://autismpdc.fpg.unc.edu/evidence-based-practices](http://autismpdc.fpg.unc.edu/evidence-based-practices)።

## ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች

**የተማሪዎች አገልግሎቶች 703-228-6061**

የት/ቤት ስነልቦና ባለሙያዎች ለእያንዳንዱ ት/ቤት በመደበኛነት ይመደባሉ። የስነልቡና ባለሙያው ከብዙ የሙያ ዘርፎች የተውጣጣ ቡድን አባል ሆነው ይሰራሉ፤ ቡድኑም ችግሮችን በመገምገም የመማር ወይም ከሁኔታ ጋር ራስን የማስተካከል ችግር ላለባቸው ተማሪዎች የጣልቃ ገብ እርምጃ እቅዶችን ያዘጋጃል። የት/ቤት ስነልቦና ባለሙያዎች በሕጻናት ስነልቦና፣ በመማር እድገትና ምዘና ላይ ልዩ ስልጠና የወሰዱ ባለፈቃድ ባለሙያዎች ናቸው። የስነልቡና ባለሙያው የተማሪዎች አስተውሎታዊ፣ ማሕበራዊና ስሜታዊ እድገት ላይ ግለሰባዊ ምዘናዎችን ሊያደርጉ፣ የተናጠል ወይም የአነስተኛ ቡድን የማማከር አገልግሎት ሊሰጡ፤ እና/ወይም ለወላጆችና ሌሎች ሰራተኞች አማካሪ ሆነው ሊሰሩ ይችላሉ። ከማህበረሰብ የአእምሮ ጤና አገልግሎት አቅራቢዎች ጋር የቅርብ ግንኙነት ተጠብቆ ይቆያል።

የት/ቤት ማሕበራዊ አገልግሎት ሰራተኞችም ለእያንዳንዱ ት/ቤት በመደበኛነት ይመደባሉ። የት/ቤት ማሕበራዊ አገልግሎት ሰራተኞች በቤት እና ት/ቤት መካከል የሚደረግ ግንኙነትን የሚያሳልጡና ለተለያዩ የማህበረሰብ ድርጅቶች እንደ አገናኝ ሆነው የሚሰሩ ባለፈቃድ ባለሙያዎች ናቸው። ከብዙ የሙያ ዘርፍ የተውጣጣ ቡድን አባላት በመሆናቸው፣ ለማሕበራዊ፣ ስሜታዊ ወይም አካዳሚክ ተግዳሮቶች አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ ጉዳዮችን ለመወሰን የተማሪዎችን አጠቃላይ ከባቢያዊ ሁኔታ ይመዝናሉ። የት/ቤት ማሕበራዊ አገልግሎት ሰራተኞች የተለያዩ የጣልቃ ገብነት አገልገሎቶችን ሊያቀርቡ ይችላሉ፤ ለምሳሌም የወላጅነት ትምህርቶች፣ የማማከር አገልግሎት፣ የአጭር ጊዜ የምክር አገልግሎት፣ ምርመራ ማድረግና ለሌሎች ኤጀንሲዎች ማስተላለፍ ይገኙበታል።
የት/ቤት ስነልቦና እና የት/ቤት ማሕበራዊ አገልግሎት ሰራተኞች አገልግሎቶችን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ ይህን ይጎብኙ:- https://www.apsva.us/student-services/school-social-workersvisiting-teachers/

**የተማሪ አገልግሎቶች:- የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት የካውንስሊንግ ፕሮግራም 703-228-6060**

ፕሮፌሽናል የት/ቤት የማማከር አገልግሎቶች በሁሉም የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ውስጥ ይቀርባሉ። ሁሉን አቀፍ የት/ቤት የማማከር ፕሮግራም ተማሪዎች በአካዳሚክ፣ ማሕበራዊ/ስሜታዊ፣ እና የስራ ዘመን እደገት መስኮች የሚኖራቸውን ስኬት ያበረታታል። ፕሮፌሽናል የት/ቤት የማማከር አገልግሎት በመማሪያ ክፍል ውስጥ ትምህርቶች አማካይነት መሰረታዊ የማማከር ፕሮግራም ያቀርባል። ለተማሪዎችም በተናጠልና በአነስተኛ ቡድን አደረጃጀት የአጭር ጊዜ ቀጥተኛ የማማከር አገልግሎቶችን ያቀርባሉ። የት/ቤት አማካሪ ባለሙያው የሁሉንም ተማሪዎች የተለያዩ ፍላጎቶች ለማሟላት ከመምህራንና ሌሎች የትምህርት ሰራተኞች፣ ከቤተሰቦችና የማህበረሰብ ኤጀንሲዎች ጋር አብረው ይሰራሉ። ለተጨማሪ መረጃ፣ እባክዎ ይህን ይጎብኙ:- https://www.apsva.us/a2e-academic-planning/ ወይም የልጅዎን ፕሮፌሽናል አማካሪ ያነጋግሩ።

**የተማሪ አገልግሎቶች:- የቤት ውስጥ ትምህርት 703-228-6051**

የቤት ውስጥ ትምህርት የተቀረጸበት ዓላማ አንድ ተማሪ ለተወሰነ ጊዜ ያህል ወደ ት/ቤት ከመምጣት የሚያግደው አካላዊ ወይም ስነ አእምሯዊ የጤና ችግሮች ኖረውበት ቤት ውስጥ ወይም የጤና እንክብካቤ ተቋም ውስጥ ተገድቦ በሚቆይበት ጊዜ የትምህርትን ቀጣይነት ለማረጋገጥ ነው።

አንድ ተማሪ ወደ ት/ቤት ለመምጣት አለመቻሉ በተፈቀደለት ሃኪም ወይም የተፈቀደለት ክሊኒካል የስነልቡና ባለሙያ መረጋገጥ ያለበት ሲሆን፣ ጥያቄውም በልዩ ፍላጎት ትምህርት ሱፐርቫይዘር መፅደቅ አለበት።

የቤት ውስጥ ትምህርትን በተመለከተ የ APS መመሪያዎችና አስፈላጊ ቅጾች በ APS ዋና ድረ ገጽ ላይ፣ Academics, Special Education, Homebound Instruction በሚለው ስር ወይም እዚህ ላይ ይገኛሉ:- http://www.apsva.us/homebound-instruction/

የቤት ውስጥ ትምህርትን የተመለከቱ ጥያቄዎች ለልዩ ፍላጎት ትምህርት ጽ/ቤት፣ የልዩ ፕሮግራሞች ክፍል በስልክ ቁጥር 703-228-6051 መቅረብ ይችላሉ።

## ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች

**የተማሪ አገልግሎቶች፡- የቋንቋ አገልግሎቶች ምዝገባ ማዕከል (LSRC) 703-228-7663**

ከእንግሊዝኛ ሌላ ቋንቋ የሚናገሩ ተማሪዎች ወደ የቋንቋ አገልግሎቶች ምዝገባ ማዕከል ተልከው የምዘና እና ምዝገባ አገልግሎት ያገኛሉ። የተማሪው የቋንቋ እና የሒሳብ ክህሎቶች ላይ በሚደረግ ምዘና እና ቀደም ሲል በነበረ የአካዳሚክ ተሞክሮ እና ከወላጅ ወይም አዋቂ ተማሪዎች በሚገኝ መረጃ መሰረት፣ የLSRC ሰራተኛ የእያንዳንዱን ተማሪ ተገቢ የክፍል ደረጃና የእንግሊዝኛ ፕሮግራም ምደባ ይወስናል። የውጭ ሃገር የትምህርት ማስረጃዎች በLSRC ተመዝነው በAPS ከሚያስፈልጉ የምረቃ መስፈርቶች አንጻር የክፍል ደረጃ እና የክሬዲት ግመታ ይሰጣቸዋል። ወላጆችና ተማሪዎችም የምዝገባ ሁኔታዎችን ከማጠናቀቅ ጋር የተያያዘ እገዛ ይደረግላቸዋል። ከአንድ በላይ ቋንቋ የሚናገሩት የ LSRC ሰራተኞች ከወላጆች ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፣ ት/ቤትና የት/ቤት ፕሮግራሞችን የተመለከተ መረጃ ይሰጣሉ፣ ለወላጆችም ገለጻ ያደርጋሉ። LSRC ለሁሉም የAPS ት/ቤቶችና ቤተሰቦች የንግግር ቋንቋ የማስተርጎምና የሰነድ ትርጉም አገልግሎት ያቀርባል።

ለተጨማሪ መረጃ፣ ቀጣዩን ድረ ገጻችንን ይጎብኙ፡- https://www.apsva.us/lsrc/።

**የተማሪ አገልግሎቶች፡- በ1973 የወጣው የተሐድሶ ሕግ ሴክሽን 504**

የአርሊንግተን ሴክሽን 504 ሒደት የተማሪዎችን ልየታ፣ ምዘና፣ ምደባ እና ስነ ስርዓታዊ ዋስትናዎችን በተመለከተ ውስን መስፈርቶች ያሉት ሲሆን፣ ይህም በ APS ት/ቤት ቦርድ ፖሊሲዎች እና በ APS ሴክሽን 504 ስነ ስርዓታዊ መመሪያ ላይ የተገለጸ ነው። በሴክሽን 504 ስር ብቁ ሊሆን የሚችል ተማሪን በቅድሚያ የመለየት ተግባር በት/ቤት ሕንጻ ደረጃ የሚካሄድ ነው። እያንዳንዱ ት/ቤት የሴክሽን 504 ኮሚቴ የሚኖረው ሲሆን በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ እውቀት ያላቸው ሰራተኞችም የኮሚቴው አባላት ይሆናሉ፡- ሴክሽን 504፤ ተማሪው (ተማሪው ሊኖርበት የሚችል አካል ጉዳትን ጨምሮ)፤ የምዘና አሰራሮች፤ መስተንግዶዎችና አገልግሎቶች፤ እና የምደባ አማራጮች። ይህ ኮሚቴ በርዕሰ መምህሩ ወይም በተወካያቸው ክትትል ስር የሚንቀሳቀስ ነው። የኮሚቴው ዓላማ ሪፈራሎችን መከወን፣ የምዘና መረጃን መዳሰስና በሴክሽን 504 ስር ብቁ እንዲሆኑ ለተወሰኑ ተማሪዎች እቅዶችን ማዘጋጀት ነው። ለሕንጻው የተመደቡት የሴክሽን 504 አስተባባሪ በሁሉም የመጀመሪያ ደረጃ የብቁነት መወሰኛ ሂደቶችና ተዘማጅ አገልግሎት ሊያስፈልግባቸው በሚችሉ ማናቸውም ስብሰባዎች ላይ እንዲሳተፉ ይጋበዛሉ።

የሴክሽን 504 ተገዢነት ኦፊሰር የፖሊሲውን ትግበራ የመከታተል ሃላፊነት ያለባቸው ሲሆን፣ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜም አድልዎ የሌለበት ችሎት ያዘጋጃሉ። የት/ቤት ቦርድ ፖሊሲ ቅጂዎችን ለማግኘት፣ እባክዎ ይህን ይጎብኙ፡- https://www.apsva.us/school-board- policies/። የሴክሽን 504 ስነ ስርዓታዊ መመሪያን ቅጂዎች ለማግኘት፣ እባክዎ ይህነ ይጎብኙ፡- https://www.apsva.us/section-504/ ወይም በቀጣዩ አድራሻ ይደውሉ ወይም ይጻፉ፡-

የተማሪ አገልግሎቶች ዳይሬክተር፣ የተማሪ አገልግሎቶች ጽህፈት ቤት የክፍል 504
የመገዛት መኮንን
Syphax Education Center
2110 Washington Boulevard
Arlington, Virginia 22204
703-228-6061

# ሌሎች ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች

**<u>የት/ቤት ጤና ቢሮ 703-228-1651</u>**

በአርሊንግተን የሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ የሚቀጠሩ የጤና ረዳቶችና የማሕበረሰብ ጤና ነርሶች የሚሰጧቸው የት/ቤት ጤና አገልግሎቶች። የት/ቤት ጤና ሰራተኞች ለተማሪዎችና ቤተሰቦቻቸው የመከላከያና የቅድሚያ ጣልቃ ገብ አገልግሎቶችን ያቀርባሉ። የእነዚህ አገልግሎቶች ግብ ተማሪው ባለው እምቅ አቅም ልክ ለመማር እንዲችል ማገዝ ነው።

1. **የት/ቤት የጤና አገልግሎቶች**

   የጤና ረዳቶች በመደበኛ የትምህርት ሰዓት በት/ቤት ክሊኒኮች ውስጥ የሚገኙ ሲሆን ለታመሙና ለተጎዱ ተማሪዎች ቀጥተኛ እንክብካቤ የሚያደርጉና መድሃኒቶችንም በማዘዣቸው መሰረት የሚሰጡ ናቸው። የድንገተኛ 911 አገልግሎቶች የሚደወልላቸው አግባብነት ሲኖረውና ጉዳዩን ወላጅ እንዲያውቀው ከተደረገ በኋላ ነው። የማሕበረሰብ አቀፍ ጤና ነርሶች እስከ ሶስት ት/ቤቶች ድረስ የተለያዩ አገልግሎቶችን ይሰጣሉ። ከሚሰጡ አገልግሎቶች መካከል፦ የጤና መረጃዎችና ክትባቶችን መከለስ፤ የጤና ችግሮች ላሉባቸው ተማሪዎች የጤና እንክብካቤ እቅዶችን ማዘጋጀት፤ ድንገተኛ መድሃኒት አሰጣጥና ልዩ የሕክምና አሰራሮችን በተመለከተ ለት/ቤቱ ሰራተኞች ስልጠና መስጠት፤ ከማሕበረሰብ ድጋፍ ሰጪዎች ጋር ማስተሳሰርና በተለያዩ የጤና ነክ ጉዳዮች ላይ ተማሪዎችን ማስተማር ይገኙበታል።

2. **የት/ቤት ጤና ሃኪም**

   የት/ቤት ጤና ሃኪም ለት/ቤት ሰራተኞችና ወላጆች የጤና ምርመራ ያደርጋሉ፣ በሁሉም የክፍል ደረጃዎች ላይ ለሚገኙና በገቢያቸው ምክንያት በቂ ለሆኑ ተማሪዎች የሚሰጥ የጤና ግምገማ ክሊኒክን ያስተባብራሉ።

3. **የማጣሪያ አሰራሮች**

   <u>የዓይን</u> እና <u>የጆሮ</u> ማጣሪያ ምርመራ ወደ አፀደ ሕጻናት ለመግባትና ለሶስተኛ፣ ሰባተኛ እና አስረኛ ክፍል ተማሪዎች፣ ለልዩ ፍላጎት ትምህርት ምዘና ለሚካሄድባቸው ተማሪዎችና በሁሉም የክፍል ደረጃዎች አዲስ ለሚገቡ ተማሪዎች በሙሉ ይደረጋል። በተጨማሪም፣ በመምህር፣ በወላጅ ወይም በሃኪም ጥያቄ መሰረት ተማሪዎች የጤና ምርመራ ሊደረግላቸው ይችላል።

4. **ሪፈራል እና ክትትል**

   የማሕበረሰብ አቀፍ ጤና ነርሶች የጤና፣ የጥርስ እና የአእምሮ ጤና እንክብካቤ ለሚፈልጉ ተማሪዎችና ቤተሰቦች ከካውንቲ እና ከማህበረሰብ ድጋፍ ሰጪዎች ጋር ዋነኛ አገናኞች ናቸው።

5. **የጥርስ ጤና**

   እያንዳንዱ ተማሪ በግል የጥርስ ሐኪም ወይም ክሊኒክ በየስድስት ወሩ የጥርስ ምርመራ እንዲያደርግ ይመከራል። ተማሪዎች ወደ አርሊንግተን DHS የጥርስ ክሊኒክ ወይም በማህበረሰቡ ውስጥ ወዳሉ የጥርስ ሕክምና አቅራቢዎች ሪፈር ሊደረጉ ይችላሉ።

6. **የጤና ሁኔታዎች**

   ወላጆች ተማሪ ልጃቸው በትምህርት ሰዓት መድሃኒት መውሰድ ወይም ሕክምና የሚያስፈልገው የጤና ችግር ካለበት ለማህበረሰብ ጤና ነርስ ማሳወቅ አለባቸው። ነርሱ ከወላጆችና የት/ቤቱ ሰራተኞች ጋር በመተባበር ለልጁ የጤና ሁኔታ ተስማሚ የሆነ ግለሰባዊ የጤና እንክብካቤ እቅድ ያዘጋጃሉ።

7. **በት/ቤት ውስጥ የሚወሰድ መድሃኒት**

   መድሃኒቶችን በትምህርት ሰዓት ለመውሰድ በሕክምና አቅራቢ የተሰጠ ማዘዣ እና በወላጆች የተፈረመ የፈቃድ መስጫ ቅጾች ያስፈልጋሉ። መመሪያዎች እና ቅጾች በእያንዳንዱ ት/ቤት ክሊኒክ ውስጥ ወይም በት/ቤት ጤና ድረ ገጽ ላይ ይገኛሉ፦ https://www.apsva.us/school-health-services/

8. **ከሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ክፍሎች ነጻ መደረግ**

   የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ላይ መሳተፍ ያለባቸው ተማሪዎች የተለየ የጤና ችግር ከሌለባቸው በስተቀር መሳተፍ አለባቸው። አንድ ተማሪ ከዚህ ትምህርት ነጻ እንዲሆን ወይም ፍላጎቱን የሚሸፍን ፕሮግራም እንዲቀርብለት ለማድረግ ከሕክምና ሰጪ የተሰጠ ማስታወሻ ያስፈልጋል።

# ሌሎች ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች

**<u>የት/ቤት ጤና ቢሮ የቀጠለ</u>**

**9. የጤና ትምህርት**

የማሕበረሰብ አቀፍ ጤና ነርሶች በመማሪያ ክፍሎች ውስጥ የተለያዩ የጤና ትምህርት አርእስት ላይ ያስተምራሉ፣ ለመምህራንም የኤክስፐርት ሙያና የጤና ትምህርት ማቴሪያሎች ምንጭ ሆነው ያገለግላሉ።

**10. የበሽታ መቀስቀስ ላይ የሚደረግ ክትትል**

የት/ቤቱ የጤና ሰራተኞች የተላላፊ በሽታዎችን መቀሰቀስ በመከታተል ምላሽ ይሰጣሉ። ከአርሊንግተን ካውንቲ የማሕበረሰብ አቀፍ ጤና ጥበቃ ቢሮ እና ከአርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች ጋር በቅርበት በመስራት በት/ቤቶችና በማህበረሰቡ ውስጥ የሕመም ስርጭትን የመመርመርና መጠኑን የመቀነስ ስራ ይሰራሉ።

# የጥናቱ ትምህርታዊ መስኮች
**K-5**

ከአፀደ ሕጻናት እስከ አምስተኛ ድረስ ባሉት የክፍል ደረጃዎች ውስጥ የጥናት ትምህርታዊ መስኮች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- የጥበብ ትምህርት
  - የዕይታ ሥነ-ጥበባት
  - አጠቃላይ ሙዚቃ

- የእንግሊዝኛ ቋንቋ ጥበባት
  - መግባባት እና መልቲሞዳል ትምህርቶች
  - ማንበብ
  - ጽሁፍ
  - ምርምር

- የጤና ትምህርት
  - ወሳኝ የሕይወት ፅንሰ ሃሳቦች
  - ጤናማ ውሳኔዎች
  - ተሟጋችነት እና የጤና ማጎልበቻ

- ሒሳብ
  - ቁጥር እና ቁጥርን መረዳት
  - ስሌትና ግመታ
  - ልኬትና ጂኦሜትሪ
  - ፕሮባብሊቲ እና ስታስቲክስ
  - ፓተርኖች፣ ተግባራትና አልጀብራ

- የሰውነት  ማጎልመሻ ትምህርት
  - የእጅና እግር እንቅስቃሴ ክህሎት እድገት
  - በሰውነት ክፍሎች ጥናት ላይ የተመሰረተ እንቅስቃሴ
  - የአካል ብቃት እቅድ ዝግጅት
  - ማሕበራዊ እና ስሜታዊ እድገት
  - የኃይል መመጣጠን

- ሳይንስ
  - ሳይንሳዊ እና ምሕንድስናዊ አሰራሮች
  - መመርመርና መገንዘብ ያሉብን ማዕከላዊ ሃሳቦች

- ማህበራዊ ጥናቶች
  - ታሪክ
  - ጂኦግራፊ
  - ኢኮኖሚክስ
  - ስነ-ዜጋ

ተማሪዎች በእያንዳንዱ የአንደኛ ደረጃ ክፍል መማር የሚጠበቅባቸው ክህሎቶችና ይዘት በቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ የማስተማር መስፈርቶች ውስጥ ይዘረዘራል።

**የክፍል ደረጃ ትምህርታዊ መስኮች ወይም ዓላማዎችን ሙሉ ይዘት ለመዳሰስ፣ እባክዎ ቀጣዩን የ APS የአንደኛ ደረጃ ስርዓተ ትምህርት ድረ ገጽ ይጎብኙ፡- www.apsva.us/instruction/curriculum-instruction/elementary-curriculum.**